''ሞት ለማናቸውም ሰው ሁሉ የተገባ
ነው የማርያም ሞት ግን ሁሉን
ያስደንቃል።''

ቅዱስ ያሬድ

# ስምዐ ጽድቅ



ስምዐ ጽድቅ

የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ማስተባበሪያ በጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እየተዘጋጀ በወር ሁለት ጊዜ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ

ጳጉሜን ፫ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. ተጀመረ

☎ 011-1553555/ 011-1553442
✉ 80078
አዲስ አበባ

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል
newspaper@eotcmk.org

## ማውጫ

፪ አጫጭር ዜናዎች
፬ መልእክት
፮ ሪፖርታዥ
፱ ቤተ አብርሃም
፲፫ ቃለ መጠይቅ
፲፮ የሕፃናት ዓምድ
፲፰ ትዝብት
፳ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ

ምክትል ዋና አዘጋጅ
ወርቅነሽ ቱፋ
ከፍተኛ ሪፖርተር
ካሣሁን ለምለሙ
ሪፖርተር
ረቂቅ መቻል
የገጽ መልክ (Layout) ዲዛይነር
ግደይ ገብሬ
ጸሐፊ
ገነት ታደሰ




ቅዱስነታቸው ከድሬ ደዋ ከተማ አስተዳደር ከንቲባና የሥራ ባልደርቦቻቸው ጋር በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽሕፈት




የድሬ ደዋ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አቶ አሕመድ መሐመድ ቡህ

# የድሬ ደዋ ከተማ አስተዳደር የመልካም ሥራ ተምሳሌት መሆኑ ተገለጠ

*በካሣሁን ለምለሙ*

የድሬ ደዋ ከተማ አስተዳደር ለቤተ ክርስቲያን እያበረከተ ባለው አስተዋጽኦ የመልካም ሥራ ምሳሌ መሆኑን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ፓትርያርክ ርእሳነ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት ገለጡ::

ቅዱስነታቸው ይህንን የገለጹት የድሬ ደዋ ከተማ አስተዳደር ከንቲባና የሥራ ባልደርቦቻቸው ለቤተ ክርስቲያን ልማትና ሰላም ላበረከቱት አስተዋፅኦ በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽሕፈት ቤት በተዘጋጀላቸው የምስጋናና የዕውቅና መርሐ ግብር ላይ ባስተላለፉት መልእክት ነው::

ቅዱስነታቸው በጽሕፈት ቤታቸው የጋበዟቸውን እንግዶች ባነጋገሩበት ወቅት የድሬ ደዋ ከተማ አስተዳደር ለቤተ ክርስቲያን እያደረገ ያለውን ሁሉን አቀፍ ድጋፍ አድንቀው ይህ መልካም ሥራ ለሌሎች ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች አርአያ ሊሆን እንደሚችል ተናግረዋል:: ‹‹ሃይማኖታችን የተለያየ ቢሆንም ፍቅራችንና አንድነታችንን አያሳሳውም ኢትዮጵያዊነታችንንም አያጠፋውም›› በማለትም አክለዋል::

እንደ ቅዱስነታቸው ገለጻ ሀገራችን የጋራ እስከሆነች ድረስ ዜጎች ሰብአዊ መብታቸው ተከብሮ በጋራ በአንድነትና በፍቅር ሊኖሩ ይገባል:: መገፋፋትና የርስ በርስ ግጭት ውስጥ መግባትን አስወግዶ ለሀገር ልማትና እድገት መሥራት ያስፈልጋል:: የሀገራችንን ሰላም፣ አንድነትና ፍቅር የምንጠብቀው በሃይማኖት ልዩነት፣ በዘርና በቀለም ሳንለያይ ከሆነ ብቻ ነው ያሉት ቅዱስነታቸው የድሬ ደዋ ከተማ አስተዳደር የሰላምና የልማት ምሳሌ መሆኑ ከተማ አስተዳደሩ ደስ ሊለው ይገባል፤ በሀገራችን ያሉ ሁሉም የፖለቲካ አመራሮች የድሬ ደዋን የመልካም ሥራ ምሳሌነት በመውሰድ ለእውነትና ለሀገር አንድነት አጥብቀው እንዲሠሩ መክረዋል::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቤቶችና ሕንፃዎች አስተዳደርና ልማት ድርጅት ኃላፊ አፈ መምህር አባ ገ/ሥላሴ ጌትነት በበኩላቸው ከዚህ ቀደም በድሬ ደዋ ከተማ አስተዳደር ተወርሰው የተመለሱ የቤተ ክርስቲያን ይዞታዎች እንዳሉ ጠቅሰው ከውርስ ከተመለሱት ቦታዎች መካከል በአንዱ ላይ ለገቢ ማስገኛ የሚውል ሕንፃ ለመሥራት ታኅሣሥ ፲፯ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም ቅዱስ ፓትርያርኩ የመሠረት ድንጋይ እንዳስቀመጡ ተናግረዋል፡፡

የድሬ ደዋ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ማትያስ በቀለ በመርሐ ግብሩ ላይ ተገኝተው ባስተላለፉት መልእክት በድሬ ደዋ ሀገረ ስብከት ላለፉት ሦስት ዓመታት ከፍተኛ የሆነ ሁከትና ብጥብጥ ውሥጥ በመቆየቱ ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን በነፃነት ሥርዓተ አምልኳቸውን ማከናወን መቸገራቸውንና የአደባባይ በዓላትንም በሥጋት ያከብሩ እንደነበር ጠቅሰው፤ "አሁን ያለው የከተማ አስተዳደር አመራር ቁርጠኛ በመሆኑ ከቤተ ክርስቲያን ጋር በሰላምና በልማት ላይ ተቀራርቦ እየሠራ ነው" ብለዋል፡፡

ሥራ አስኪያጁ አያይዘውም "የድሬ ደዋ ከተማ አስተዳደር በተለይ ዘንድሮ ፴ ሺህ ካሬ ሜትር በላይ መሬት ለአደባባይ በዓላት ማክበሪያነት እንዲውል ከመስጠቱ ባሻገር የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ ያልነበራቸው የቤተ ክርስቲያን ይዞታዎች ሁሉ የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ እንዲኖራቸው አድርጓል›› ብለዋል፡፡

ሀገረ ስብከቱ የመካነ መቃብር እጥረት እንዳለበት ለከተማ አስተዳደሩ ባቀረበው ጥያቄ መሠረትም በቅርቡ ለመካነ መቃብር የሚውል ተጨማሪ መሬት እንደሚሰጥ ያስታወቁት ሥራ አስኪያጁ "ሌሎች ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ከድሬ ደዋ ከተማ አስተዳደር በመማር መንግሥትና የእምነት ተቋማት በጋራ መሥራታቸው ለሀገር ሰላምና ልማት ሊኖረው የሚችለውን ድርሻ ሊገነዘቡ ይገባል" ብለዋል፡፡

በዚሁ የዕውቅናና ሽልማት መርሐ ግብር ላይ የተገኙት የድሬ ደዋ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አቶ አሕመድ መሐመድ ቡህ ከተማ አስተዳደራቸው ለቤተ ክርስቲያን ባበረከተው አስተዋጽኦ የምስጋናና የዕውቅና ሽልማት ማግኘታቸው እንዳስደሰታቸው ገልጠው ቤተ ክርስቲያን የሰጠቻቸው ዕውቅና ለበለጠ መልካም ሥራ እንዲነሳሱ እገዛ እንደሚያደርግላቸው ተናግረዋል፡፡

"ቤተ ክርስቲያን ለሀገራችን የኪነ ሕንፃ ጥበብ እድገት ያበረከተቻቸውን አስተዋጽኦ ያደነቁትና ለተደረገላቸው መስተንግዶና አቀባበል እንዲሁም ለተሰጣቸው የዕውቅና ሽልማት ምስጋናቸውን ያቀረቡት የድሬ ደዋ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ልዩ አማካሪና የድሬ ደዋ ከተማ አስተዳደር ብልፅግና ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ መብራት ገብረየስ ናቸው፡፡

# በሙዚቃ ድግስ የታጀቡ የቤተ ክርስቲያን በዓላት ከየት ወዴት?

መነሻቸውም ሆነ መድረሻቸው የክርስትና ሃይማኖትና አስተምህሮ የሆኑት፣ በተለይም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መገለጫ የሆኑትንና በምእመኑ ዘንድ በጉጉት የሚጠበቁ በዓላት በዓለማዊ ኮተት እንዲታጀቡ መደረግ ከጀመሩ ሰንብተዋል። በቤተ ክርስቲያናችን እና በምእመናን ዘንድ ልዩ ትኩረት የሚሰጣቸው የዘመን መለወጫ፣ ገና፣ ጥምቀት እና የትንሣኤ በዓላት ቀደም ሲል የገበያ ማሻሻጫ አሁን አሁን ደግሞ የዘፈን እና የመዝናኛ ማጀቢያ እንዲሆኑ የተፈረደባቸው ይመስላል።

ቀደም ባሉት ዓመታት የዘመን መለወጫ፣ የገና፣ የጥምቀትም ሆኑ የትንሣኤ በዓላት ሲደርሱ በዓላቱን በማስታከክ በመስቀል የአደባባይ ኤግዚብሽን ማዕከል ይደረግ የነበረው ዝግጅት ገበያ ብቻ እንደነበር ይታወቃል። በተለይ ገዢና ሻጭ የሚገናኝበት፣ ከወትሮው በተለየ መልኩ ሌላ ጊዜ እና ቦታ ውድ የሆኑ ነገሮች በርካሽ የሚገኙበት በየቦታው እንደልብ የማይገኙ የምግብ ዓይነቶች እና ልዩ ልዩ ቁሳቁሶች በአንድ ቦታ ለተጠቃሚው የሚቀርቡበትም ነበሩ። ከላይ እንደተጠቀሰው ገበያው የሚካሄደው በበዓላቱ ስም መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ማለት ነው።

የቤተ ክርስቲያናችን መገለጫ በሆኑት በዓላት ስም እና በበዓላቱ ወቅት የሚከናወኑት እነዚህ የገበያ ዝግጅቶች ባለቤቶች እነማን እንደሆኑ አይታወቁም፤ ቤተ ክርስቲያንም በበዓላቷ ስም የሚነግዱትን አካላት ማንነት ጠይቃ አታውቅም። የማያምነውም ሆነ አማኙ ክፍል በሚታደምበት በዚህ በዓል ጠበቅ ንግድ ተሳታፊዎቹ ወይም ባለቤቶቹ ኦርቶክሳውያን ይሁኑ የሌላ እምነት ተከታዮች ጠያቂ ኖሮባቸው አያውቅም። መድረኩ ፈለጊና ተፈላጊን በቀላሉ የሚያገናኝ ነው ተብሎ በአዎንታዊ መልኩ ቢወሰድም እየዋለ ሲያድር ያስከተለው አሉታዊ ተፅዕኖ ግን ቀላል አይደለም።

በዓላቱ ዛሬ ዛሬ ታላላቅ የሙዚቃ ድግሶች የሚዘጋጅባቸው መድረኮች ሆነዋል። ከበዓላቱ ስምና ተግባር በተቃራኒ ለዓለማዊ አገልግሎት ሲውሉ ለምን ባይ ጠያቂ የለባቸውም። ከቤተ ክርስቲያን ውጪ በሆኑ ሰዎች በገበያ የተጀመረው በዓል ተኮር ትዕይንት ወደ ኮንሰርትነት (የሙዚቃ ድግስነት) ሲቀየር ለምን የሚል ጠያቂ ሊኖር ይገባል። በዓላቱ የሚከበሩበት የራሳቸው የትመጣና አስተምህሮ እንዳላቸው ገልጦ ፊት ለፊት ማስተማር አስፈላጊ ነው። በሙዚቃና በዳንኪራ የታጀቡ የቤተ ክርስቲያንንመ አስተምህሮ በሚያጠለሹ መድረኮች ላይም ባለመገኘት ወይም ባለመታደም ክብሯን ማስጠበቅ ከቤተ ክርስቲያን ልጆች ይጠበቃል።

በእርግጥ አሁን አሁን በገና ፣ በጥምቀትና በትንሣኤ ዋዜማ ላይ የበዓላቱን ስም ታክው የሚከወኑ ልዩ ልዩ ዝግጅቶች በሌሎች የእምነት በዓላት ስምም መዘጋጀት ጀምረዋል። ነገር ግን እንደ ገና እና ትንሣኤ የሙዚቃ ኮንሰርት ማጀቢያ ሲደረጉ ግን አይታይም። ይህ የሚያሳየው ለቤተ ክርስቲያን እና ለበዓላቷ አዘጋጆቹ ወይም ባለቤቶቹ ያላቸውን ንቀት ነው። በሌሎች ሃይማኖቶች በዓላት ላይ የንግድ ባዛር ሲተዋወቅ እና ሲካሄድ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን በዓላት ግን የኮንሰርት(የሙዚቃ ድግስ) ማድመቂያ፣ አዲስ የዘፈን አልበም እና ዘፋኝ ማስታወቂያ ናቸውና ክርስቲያኖች ልብ ልንለው ይገባል።

ዛሬ በዓላቱን ጠብቀው ዘፈን መልቀቃቸው፣ ኮንሰርት (የሙዚቃ ድግስ) ማዘጋጀታቸው ብቻ አይደለም መታየት

ያለበት፡፡ በጊዜ ሂደት ትውልዱ አዲስ ዓመት ሲመጣ ራሱን በንስሐ ከማደስ ይልቅ በዘፈን ስለመታደስ እንዲያስብ እየተደረገ ነው፡፡ ገና ሲመጣ ስለ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ ሳይሆን ስለሚዝናናበት ኮንሰርት (የሙዚቃ ድግስ) እንዲናፍቅ እየተደረገ ነው፡፡ ጥምቀት ሲመጣ ትውልዱ ስለተከበረው የሰው ልጅ መንፈሳዊ ድኅነት ከማሰብ ይልቅ በዓሉን ጠብቆ አዲስ ስለሚለቀቀው የዘፈን አልበም እንዲያስብ እየተጋበዘ ነው፡፡ የተከበረውን በዓል ሳይሆን በዓሉን ታኮ ስለሚመጣው የሥጋ ደስታ ላይ ዓይኑ እንዲያማትር የልምምድ መድረክ እየተመቻቸ ነውና የቤተ ክርስቲያን ልጅ የሆነው ሁሉ ከዚህ ወጥመድ መሸሽ ተገቢ ነው ሌሎችንም ከወጥመዱ እንዲሸሹ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

**በዓላቱ ዛሬ ዛሬ ታላላቅ የሙዚቃ ድግሶች የሚዘጋጅባቸው መድረኮች ሆነዋል። ከበዓላቱ ስምና ተግባር በተቃራኒ ለዓለማዊ አገልግሎት ሲውሉ ለምን ባይ ጠያቂ የለባቸውም። ከቤተ ክርስቲያን ውጪ በሆኑ ሰዎች በገበያ የተጀመረው በዓል ተኮር ትዕይንት ወደ ኮንሰርትነት (የሙዚቃ ድግስነት) ሲቀየር ለምን የሚል ጠያቂ ሊኖር ይገባል።**

የነገውን ጥፋት በጥልቀት አይቶ ከክፉው ጋር ላለመተባበር ከመራቅ ውጪ ቤተ ክርስቲያን በዓላቷን አጉልታ የምታሳይበትን መድረክ መፍጠምር ይጠበቅባታል፡፡ የዘፈን ማድመቂያ የሆኑትን በዓላት ዝማሬ የሚሰማባቸው ሳምንታት በማድረግ ትክክለኛ ገጽታቸውን መመለስ ከእምነቱ ተከታዮች ይጠበቃል፡፡ በዓላቱን የሚገልጹ መንፈሳዊ ነገሮችን ለገበያ በማቅረብ በሰው ልብ ታትመው እንዲቀሩ ሰፊ ሥራ መሥራትም ይኖርበታል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተጀመሩት በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ብቻ ተወስነው የሚታዩት ትናንሽ የንግድ እንቅስቃሴዎች በደንብ ተደራጅተው ትልቅ ሥራን ወደ መሥራት እንዲሸጋገሩ ቢደረግ በተለይ በዘፈንና በማስታወቂያ ከሚያደነቁሩት የገበያ ማዕከላት ልጆቿን አውጥታ የበዓላቱን ክብር በምትገልጥባቸው ትምህርትና መንፈሳዊ ዝማሬዎች የደመቁ የገበያ ማዕከላትን በየአጥቢያው ብትከፍት ከላይ ለተዘረዘሩት ችግሮች መፍትሔ ማግኘት ይቻላል ብለን እናምናለን፡፡ በሌላም አገላለጽም በዓላቱን ጠብቀው እና በኅብረት ሆነው ትልቅ መንፈሳዊ ባዛር በማዘጋጀት ከየሰው አእምሮ ሊጠፋ የተዘጋጀውን የቤተ ክርስቲያን ዕሴት በቀላሉ መመለስ ይቻላል፡፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዘማርያን እንዲሁም ሰባክያን በሕብረት በመሆን በኮንሰርት (በሙዚቃ ድግስ) የተወሰደውን ሰው መመለስ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ኦርቶዶክሳውያን ነጋዴዎች በመተባበር በበዓላቸው ላይ ምርቶቻቸውን ለምእመናን የሚሸጡበትን መድረክ ቢያመቻቹ ራሳቸውን ብሎም የምእመኑን ሥጋዊና መንፈሳዊ ሕይወት መጥቀም ጭምር ነው፡፡

የቤተ ክርስቲያንን በዓላት ጠብቀው የሚዘጋጁ ኢ-ክርስቲያናዊ ተግባራት በቀጣይ ወዴት ሊያመሩ እንደሚችሉ መገመት አያዳግትም፡፡ ከኤግዚቢሽን ማዕከል ወደ ሆቴሎች የተዛመተው በበዓላት ስም የሚዘጋጀው የመሙዚቃ ኮንሰርት ቀስ በቀስ በግለሰቦች ስም ላለመዘጋጀቱ ምን ዋስትና አለ? የእስከዛሬው የሚያሳየን ይህን ነውና፡፡ ‹‹ሳይቃጠል በቅጠል›› እንዲሉ ነገ ከፍቶ የሚመጣውን ዛሬ ላይ በመቅጨት ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን የነገ ክብር እና ህልውና ዛሬ ላይ አጥብቀን እንሥራ እንላለን፡፡

# ገዳማትን ከጊዜያዊ ድጋፍ የማውጣት አስፈላጊነት

*በካሣሁን ለምለሙ*



የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የጥንታዊና ታሪካዊ ገዳማት ባለቤት ናት፡፡ በመላ ሀገሪቱ በርካታ ጥንታውያን ገዳማት የሚገኙ ሲሆን በእነዚህ ገዳማት ውስጥ የበቁና ዓለምን የናቁ አባቶችና እናቶች በአንድነት ተሰባስበው ገዳማዊ ሕይወትን ይመራሉ፡፡ መታረዝ፣ መራብ፣ መጠማትና መውጣት መውረድ ለእነሱ የዘወትር ክብራቸው ነው፡፡ ድንጋይ ተንተርሰው ጤዛ ልሰው ሕይወትን በመምራት የክርስቶስን መንግሥት ይናፍቃሉ፡፡ ይሁን እንጅ እነዚህ ገዳማውያን የሚኖሩባቸው አንዳንድ ገዳማት በከፋ የኢኮኖሚና የመሠረተ ልማት ችግር ውስጥ ይገኛሉ፤ ቢሆንም ገዳማቱ ያሉባቸውን ችግሮች ለመፍታት ቤተ ክርስቲያን ከሞላ ጎደል ያቅሟን እያደረገች ትገኛለች፡፡ ከአቅም በላይ የሆነውን ደግሞ በጎ አድራጊ ምእመናንን በማስተባበር ገዳማቱ በሚደገፉበት ሁኔታ ላይ ስትሠራ ቆይታለች፡፡

በዚህ ረገድ አንዳንድ ገዳማት ከችግራቸው ወጥተዋል፤ በርካቶቹ አሁንም ድረስ በከፍተኛ ችግር ወስጥ ይገኛሉ፡፡ የገዳማቱን ችግር ለመፍታት በማኅበረ ቅዱሳን በኩል በርካታ ስልቶች ተነድፈው ወደ ሥራ ከተገባ ዓመታት አልፈዋል፡፡ ማኅበሩ ከአባላቱ ከሚያገኘው ገቢ በተጨማሪ በጎ አድራጊዎች ምእመናንን በማስተባበር ፕሮጀክት ቀርጾ ገዳማቱን ሲደግፍና ሲያግዝ ቆይቷል፡፡ የዚህ በጎ ተግባር ማሳያ ከሆኑት አንዱ ፈለገ ጥበብ ዶ/ር ዓለማየሁ ዋሴ ለማኅበሩ በስጦታ የሰጡትን "እመጓ" የተሰኘውን መጽሐፍ በመሸጥ በገቢው የሰባት ያህል ገዳማት ፕሮጀክቶች ፍጻሜያቸውን እንዲያገኙ አድርጓል፡፡

ከመጽሐፉ ሽያጭ የተገኘው ከ፬.፰ ( አራት ነጥብ አምስት) ሚሊዮን ብር በላይ ለሰባት ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ መሆኑንና ፕሮጀክቶቹ መጠናቀቃቸውን አስመልክቶ እንዲሁም ለፈለገ ጥበብ ዶ/ር ዓለማየሁ ዋሴ ዕውቅና ለመሥጠት ጥር ፪ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም በባሕር ዳር ዩኒሰን ሆቴል በተዘጋጀው መርሐ ግብር ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንን ጨምሮ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶችና የመንግሥት ባለሥልጣናት የተገኙ ሲሆን በመርሐ ግብሩ ከተገኙት የመንግሥት ባለሥልጣናት መካከል የባሕር ዳር ዩኒቨርስቲ ፕሬዝዳንት የሆኑት ዶ/ር ፍሬው ተገኘ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ኢትዮጵያን በትምህርት ሚኒስትርነት እንዳገለገለች አስታውሰው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥር የሚተዳደሩ ገማትን ከጊዜያዊ ድጋፍ በማውጣት ቋሚ የሆነ የገቢ ምንጭ ሊፈጠርላቸው እንደሚገባ አስገንዝበዋል፡፡ ዶ/ር ፍሬው አክለውም ፈለገ ጥበብ ዶ/ር ዓለማየሁ ዋሴ "እመጓ" የተባለውን መጽሐፍቸውን ለቤተክርስቲያን በሥጦታ በማበርከት ከመጽሐፉ ሽያጩ የተሰበሰበው ገቢ ለሰባት የተለያዩ ገዳማት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ እንዲሆን ማድረጋቸው ለቤተ ክርስቲያን፣ ለምእመናንና ለመንግሥት ትልቅ የቤት ሥራ የሠጠ ተግባር ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ዘመናዊ የትምህርት ተቋማት ከመንፈሳዊ የዕውቀት ተቋማት ጋር ተለያይተው ሥራ መጀመራቸው አሁን በሀገራችን ለምናየው ምስቅልቅል መንሥኤ መሆኑን የጠቀሱት ፕሬዝዳንቱ ለዚህ ሀገራዊ ችግር መፍትሔ ለመስጠትም ሀገራዊ ዩኒቨርሲቲዎች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለሀገር በቀል ዕውቀት ከፍተኛ ትኩረት እየሰጡ መሆናቸውን

ጠቁመው የባሕር ዳር ዩኒቨርስቲም ለወደፊቱ ከገዳማት ጋር በጋራ እንደሚሠራ አረጋግጠዋል።

ሌላው በመርሐ ግብሩ ላይ የተገኙት የአማራ ክልል ደራስያን ማኅበር ፕሬዚዳንት ሊቀ ኅሩያን በላይ መኮንን ፈለገ ጥበብ ዶ/ር ዓለማየሁ ዋሴ የመጀመሪያ መጽሐፋቸውን በስጦታ በመለገስ የኢኮኖሚና የመሠረተ ልማት ችግር ያለባቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ገዳማት እንዲረዱበት ማድረጋቸው የሚያስመሰግንና ለሌሎችም ትምህርት የሚሆን ነው ያሉ ሲሆን መጽሐፉ እጅግ ተነባቢ በመሆኑ ከንባብ ባህል ርቆ የቆየውን ትውልድ ወደ ንባብ ባህል እንዲመለስ ያደረገ መጽሐፍ እንደሆነም አስረድተዋል።

የአማራ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ መላኩ አላምረው በበኩላቸው "አንዳንድ መጻሕፍት የጥላቻ ሐውልትን የሚተክሉ ሲሆኑ እንደፈለገ ጥበብ ዶ/ር ዓለማየሁ ዋሴ ዓይነቱ መጽሐፍ ደግሞ ለአንባብያን የሥጋና የመንፈስን ዕውቀት ከመጨመራቸው ባሻገር የሚለካ መልካም ውጤትም ያስገኛሉ" ብለዋል። በሀገራችን በአብዛኛው ለቱሪስት መስህብነት የሚያገለግሉት ጥንታዊና ታሪካዊ ገዳማት እንደሆኑ የጠቆሙት ኃላፊው ገዳማቱ የጎብኚዎቻቸው ቁጥር እንዲጨምርና በገቢ ራሳቸውን እንዲችሉ የማድረግ ሥራ እየተሠራ እንደሆነም ተናግረዋል።

በዕለቱ ተገኝተው ቃለ ምዕዳን የሰጡት የባሕር ዳር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ አብርሃም የገዳማትን ችግር መፍታት የቤተ ክርስቲያን ድርሻ ብቻ ማድረግ ተገቢ እንዳልሆነ አንሥተው ገዳማትና የአብነት ትምህርት ቤቶች የሀገር መሠረቶች በመሆናቸው የአሁኑ ትውልድ እነዚህን የሀገር መሠረቶች ጠብቆና ተንከባክቦ ለመጭው ትውልድ የማስተላለፍ ኃላፊነት እንዳለበት አስረድተዋል።

ዘመን ከዷቸው ተሸፍነው የቆዩ ገዳማት "እመን" በተሰኘው የፈለገ ጥበብ ዶ/ር ዓለማየሁ ዋሴ መጽሐፍ አማካይነት መተዋወቃቸውና ከመጽሐፉ ሽያጭ የተገኘው ሙሉ ገቢም ችግር ላይ ለወደቁ ሰባት ገዳማት ፕሮጀክት መፈጸሚያ መዋሉ አስደሳች እንደሆነ የተናገሩት ብፁዕነታቸው ሕንጻ ቤተ ክርስቲያናቸው ያልታደሱ ገዳማት እንደገና ታድሰው፣ የዕለት ጉርስ የዓመት ልብስ የሌላቸው ገዳማውያንም ምግብና ልብስ አግኝተው የተጠናከረ ገዳማዊ ሕይወትን እንዲመሩ መሠራት እንዳለበት አስገንዝበዋል። እጅግ አስተማሪዎች፣ ትውልድን የሚማርኩ፣ የትውልዱን ማንነት የሚገነቡ የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ የሚያስረዱ፣ ትወልድንም በሥነ ምግባር የሚያንጹ የጽሑፍ ሥራዎች ሊሠሩ እንደሚገባም ብፁዕነታቸው መክረዋል።

ብፁዕነታቸው አያይዘውም ‹‹ማኅበረ ቅዱሳን በገዳማት ላይ እየሠራ ያለው መልካም ሥራ ተጠናክሮ እንዲቀጥል አሳስበው ከዚህ በፊት ብዙ ሠርቷል፤ ብዙም እየሠራ ነው፤ ወደፊትም ብዙ እንደሚሠራ እናምናለን›› ብለዋል። የእመን መጽሐፍ ደራሲ ፈለገ ጥበብ ዶ/ር ዓለማየሁ ዋሴ በዕለቱ ባስተለፉት መልእክት አብዛኞቹ የቱሪስት መዳረሻዎች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሀብቶች መሆናቸውን አስረድተው እነዚህ የቱሪስት መዳረሻዎች የትውልዱን ሞራል ከመገንባት ባሻገር መንፈሳዊ ርካታን የሚሰጡ ቦታዎች ናቸው ካሉ በኋላ የገዳማቱን ገቢ በመጨመር ራሳቸውን የሚችሉበትን መንገድ ማመቻቸት ያስፈልጋል ብለዋል።

ደራሲው አያይዘውም ኢትዮጵያ ከሌሎች ተቋማት ከምታገኘው ገቢ ይልቅ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከሚተዳደሩ መንፈሳዊ ቅርሶችና የቱሪስት መስሕቦች የምታገኘው ገቢ ይበልጣል ካሉ በኋላ ሀገሪቱ ከምንጊዜውም በበለጠ ገቢ ለመሰብሰብ መንግሥት ገዳማቱን መንከባከብ፣ ማደስ እንዲሁም ራሳቸውን በገቢ እንዲችሉ ማገዝ እንደሚጠበቅበት አሳስበዋል። አክለውም ይህ ተግባር የመንግሥትና የቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን የሀገሪቱ ዜጎች ድርሻ ሊሆን እንደሚገባም በመጠቆም። ‹‹እኔ ባለኝ አቅም የድርሻዬን ለመወጣት በማሰብ ጥሬ ገንዘብ የመሥጠት አቅም ባይኖረኝም የመጀመሪያ መጽሐፌ የሆነውን "እመን" መጽሐፍ ለገዳማት ማጠናከሪያ እንዲሆን በሥጦታ አበርክቻለሁ›› ያሉት የመጽሐፉ ደራሲ ፈለገ ጥበብ ዶ/ር ዓለማየሁ ‹‹መጽሐፉን ለማኅበረ ቅዱሳን በኃላፊነት መስጠቴ ከመጽሐፉ ሽያጭ

የተገኘው ከ፬.፰ ( አራት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ብር) በላይ ለሰባት ገዳማት ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ መዋሉ በትንሹም ቢሆን ክርስቲያናዊ ግዴታዬን እንደተወጣሁ እንዳስብ አድርጎኛል›› ብለዋል፡፡ የእመጓ መጽሐፍ ሽያጭ ገቢ ሰባት ገዳማትን መርዳት ከቻለ ሁሉም የድርሻውን ቢወጣ መንፈሳዊ ቦታዎች ተጠብቀው ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፍ የሚያስችል ተግባር እንደሚሠራ ገልጸዋል፡፡

በማኅበረ ቅዱሳን የቅዱሳት መካናት መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶች አገልግሎት ማስተባበሪያ ም/ኃላፊ ዲ/ን አንድነት ተፈራ በመርሐ ግብሩ ላይ ተገኝተው ባቀረቡት ሪፖርት የአብነት ትምህርት ቤቶች መምህራንና ተማሪዎቻቸው እንዲሁም ገዳማውያን ማንኛውም ዜጋ ከመንግሥት የሚያገኘውን ማኅበራዊ አገልግሎት እያገኙ ባለመሆናቸው ቤተ ክርስቲያን ልጆቿን አስተባብራ የማኅበራዊ አገልግሎት ተቋማትንና መሠረተ ልማቶችን ተደራሽ እንደምታደርግ ተናግረዋል፡፡

ፈለገ ጥበብ ዶ/ር ዓለማየሁ ዋሴ የመጀመሪያ መጽሐፋቸው የሆነውን እመጓ መጽሐፍ ለማስተባበሪያው በስጦታ ሰጥተው ከመጽሐፉ ሽያጭ የተገኘው ከ፬.፭ (አራት ነጥብ አምስት) ሚሊዮን ብር በላይ ለአርብዓ ሐራ መድኃኔ ዓለም ገዳም የአብነት ተማሪዎች ማደሪያ ሕንፃ ፣ ለናዳ ቅድስት ማርያም ገዳም ለእርሻ ትራክተር መግዣ፣ ለእመጓ ቅዱስ ዑራኤል ለልማት አገልግሎት የሚውል የከተማ ቦታ መግዣ፣ ለአምስቲያ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የመጠጥ ውኃ ፕሮጀክት፣ ለዋሻ አቡነ እንድርያስ የወፍጮ ፕሮጀክትና ለግሽ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳም ሙዚየም ግንባታ እንደዋለ በሪፖርቱ አብራርተዋል፡፡

ም/ኃላፊው አያይዘውም ፈለገ ጥበብ ዶ/ር ዓለማየሁ ዋሴን እንደ አብነት በማየት ምእመናንም ሆኑ የሀገር ቅርስ ይመለከተኛል የሚሉ ሁሉ ገዳማት በገቢ ራሳቸውን እንዲችሉ በሚደረገው ተግባር ሁሉ ተሳታፊ እንዲሆኑ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

**የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ኢትዮጵያን በትምህርት ሚኒስትርነት እንዳገለገለች አስታውሰው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥር የሚተዳደሩ ገማትን ከጊዜያዊ ድጋፍ በማውጣት ቋሚ የሆነ የገቢ ምንጭ ሊፈጠርላቸው እንደሚገባ አስገንዝበዋል፡፡**

# ብፁዕ አቡነ ገብርኤል (ዶ/ር) ሊቀ ጳጳስ ከ፲፱፻፴፫-፳፻፲፫ ዓ.ም

**ክፍል ሁለት**



ብፁዕ አቡነ ገብርኤል (ዶ/ር) ሊቀ ጳጳስ

**በመጽሐፈ ሲራክ**

የተወደዳችሁ አንባብያን የዚህን ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል ከዚህ በፊት በነበረው እትም ላይ ማቅረባችን ይታወሳል፡፡ ቀጣዩንና የመጨረሻውን ክፍል ደግሞ እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡

ብፁዕ አቡነ ገብርኤል ከ፲፱፻፷፫ ዓ.ም ጀምሮ እስከ ፳፻ ዓ.ም ድረስ ‹‹በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል ተመድበው ጥንታውያን ገዳማትን አስተዳድረዋል›› በሚለው ዐረፍተ ነገር የዓ.ም ስሕተት አለበት፡፡ ብፁዕነታቸው በኢየሩሳሌም የቆዩት ለ፲ ዓመት ሳይሆን ከ፲፱፻፷፫ ዓ.ም ጀምሮ እስከ ፲፱፻፷፮ ዓ.ም ለ፫ ዓመት ከ፮ ወር ነው፡፡ ቀሪውን ማለትም ከ፲፱፻፷፮ ዓ.ም አጋማሽ ጀምሮ እስከ ፳፻ ዓ.ም ድረስ ያለውን ጊዜ የቆዩት ደግሞ አሜሪካን ሀገር መሆኑን እየገለጽን ለተፈጠረው ስሕተት ይቅርታ እንጠይቃለን፡፡

ብፁዕነታቸው የመጀመሪያ፣ ሁለተኛና ሦስተኛ ዲግሪያቸውን በሩሲያና በአሜሪካን ተምረው እዚያው ኮሌጅ ተመድበው የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናትን ታሪክ በማስተማር ላይ ነበሩ፡፡ በ፲፱፻፷፱ ዓ.ም ለይፋዊ ጉብኝት እና ስብሰባ ወደ ሩሲያ በሄዱት ሦስተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ጥሪ እንደተደረገላቸው አውስተናል፡፡ በጊዜው የቅዱስነታቸውን ጥሪ ተቀብለው ወደ ሀገር ቤት የመጡት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ገብርኤል (ዶ/ር)ወቅቱ በ፲፱፻፷፱ ዓ.ም ቀይ ሽብር የሚካሄድበትና ብዙ ሰው የሚገደልበት ወቅት ስለነበር በተለይም በሀገራችን ታላቅ ሕዝባዊ ቀውስ ስለነበር ሰዎች እዚያው እንዲቀሩ ቢለምኗቸውም የቅዱስ ፓትርያርኩን ‹‹ሀገርህ ትፈልግሃለች ›› ጥሪ ችላ ብለው ጥሪያቸው ማርኳቸው ወደ ሀገር እንደተመለሱ የሕይወት መቅረት እንዳልቻሉ ይልቁንም አባታዊ ፍቅራቸውና ታሪካቸው ይናገራል፡፡

መንፈሳዊ አገልግሎትን በዚያው በመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት የጀመሩት ብፁዕ አቡነ ገብርኤል (ዶ/ር) ሊቀ ጳጳስ እስካረፉበት ኅዳር ወር ፳፻፲፫ ዓ.ም ድረስ ቤተ ክርስቲያንን በቅንነት በሙሉ አቅማቸው፣ በገንዘባቸውና በጉልበታቸው ሲያገለግሉ ኖረዋል፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን ዋና ጸሐፊ ሆነው በሚሠሩበት ጊዜም ብዙ መንፈሳዊ ሥራዎችን አከናውነዋል፡፡ በአምስት ክፍላተ ሀገራት የካህናት ማሠልጠኛ እንዲከፈቱ አድርገዋል፤ካህናት

በስብከተ ወንጌልና በሌሎችም የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እንዲሳተፉ እና ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግም ችለዋል፡፡ ቤተ ክርስቲያን በብዙ መንገድ ራስዋን እንድትችል መንፈሳዊነቷን ጠብቃ መዘመን ይገባታል የሚለውን ሐሳብ ያራምዱ የነበሩት ብፁዕነታቸው ይህን በጎ ሐሳባቸውን በተመደቡበት ቦታ ሁሉ ለመተግበር ሞክረዋል፡፡ በተለይ እርሳቸው ተመድበው ባገለገሉባቸው መምሪያዎች ለምሳሌ የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን፣ የትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት እንዲሁም በመንበረ ፓትርያርክ የሕዝብ ግንኙነትና የውጭ ጉዳይ መምሪያ ቀደም ብለው የተቋቋሙ ሆነው ሳለ እንደ ዕድሜያቸው እድገት እና ለውጥ አለማሳየታቸውን በቁጭት ይናገራሉ፡፡ በተመደቡበት የሥራ መስክ ለውጥን ለማምጣት ከሚያደርጉት ጥረት ባሻገር ቤተ ክህነቱ አምባገነናዊና ዝርክርክ አሠራርን እንዲያስወግድ፣ የቤተ ክህነትንና የቤተ ክርስቲያንን የሥራ ችግር ሊፈታ የሚችል ሥር ነቀል የሆነ የአሠራርና የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲሁም ዘመኑን የተከተለ የአስተዳደር ዘይቤ ያስፈልጋል በማለት በግልጽ ይናገሩ ነበር፡፡

ብፁዕነታቸው የኤርትራ ክፍለ ሀገር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በመሆን ከአንዴም ሁለት ጊዜ ባገለገሉባቸው ዓመታት ሕዝቡን ከማስተማርና ከማጽናናታቸው ባሻገር ዘርፈ ብዙ የልማት ሥራዎችን ሠርተዋል፡፡ ‹‹እግዚአብሔር የለም›› በሚለው የደርግ ሥርዓት ውስጥ ቤተ ክርስቲያንን እና ኢትዮጵያን በተመለከተ ደርግን ፊት ለፊት በድፍረት በመናገር፣ በመገሠጽ እንዲሁም በመምከር አባታዊ ግዴታቸውን ተወጥተዋል፡፡ በ፲፱፻፸፬ ዓ.ም በደርግ እና በሻዕቢያ መካከል እየተፋፋመ በመጣው ጦርነት ሳቢያ በነበረው ስብሰባ ላይ የተገኙት ብፁዕነታቸው ከሌሎች በተለየ የሀገሪቱን መሪ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያምን ‹‹ጦርነት ቆሞ ሰላምና ዕርቅ ሊወርድ ይገባል፣ እልቂቱንም አንደግፍም›› በማለት ፊት ለፊት ሞግተዋል፡፡ በኋላ ላይ የተነሣውንና ተግባራዊ የሆነውን የኤርትራን መገንጠል ጉዳይ “ኤርትራ አንገት ናት አትገነጠልም” በማለት እንደ አንድ መንፈሳዊ አባት የኢትዮጵያውያንን የመንፈስና የሥጋ ትስስር እንዲሁም ለዘመናት የቆየ አንድነት አስተጋብተዋል፡፡

በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ዘመነ ፕትርክና በቅዱስነታቸውና በቅዱስ ሲኖዶስ ትእዛዝም በካሪቢያን ሀገራት ሊቀ ጳጳስ ሆነው በመመደብ አገልግለዋል፡፡ በጊዜው በውጭው ዓለም ሲኖዶስ የመመሥረት ሙከራ እና እንቅስቃሴ ስለነበር ቤተ ክህነቱ ለሁለት እንዳይከፈል ሕዝቡን በማረጋጋት የመንፈሳዊ አባትነት ኃላፊነታቸውን ተወጥተዋል፡፡ በዚያም ለ፳ ዓመታት ሲያገለግሉ የቆዩት አባት ኤጲስ ቆጶስ እንዲኾኑ ለፓትርያርኩና ለቅዱስ ሲኖዶሱ ጥቆማ በማቅረብ ወደ አዲስ አበባ በመማጣት በሢመተ ጵጵስና ብፁዕ አቡነ ታዴዎስ ተብለው ተሰይመው ወደ ትሪናዳድና ቶቤጐ እንዲሄዱ አድርገዋል፡፡ የካሪቢያንና ላቲን አሜሪካ ሀገሮችን (ሀገረ ስብከት) መንበርንም ለእርሳቸው በማስረከብ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ወጥነት ባለው መልኩ እንዲካሄድ በማድረግ እና አባታዊ ተልእኮአቸውን በመወጣት ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰዋል፡፡

ብፁዕነታቸው በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም በነበራቸው የሦስት ዓመት አገልግሎት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ጥንታውያን ገዳማትን አስተዳድረዋል፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም ባላት ገዳማት ላይ ባለ መብት እንድትሆን በጊዜው ከነበሩት የኢትዮጵያ አምባሳደር በእስራኤል እንዲሁም ከእስራኤል መንግሥት ጋር ብዙ ሠርተዋል፡፡ በተለይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ርስት የሆነው የዴር ሡልጣንን ጉዳይ ለቅዱስ ሲኖዶስ በማቅረብ ቅዱስ ሲኖዶስ ተወያይቶበት ጉዳዩን የሚከታተሉ የመንግሥት እና የቤተ ክርስቲያን አካላት ያሉበት ኮሚቴ እንዲቋቋም አስደርገዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከመንግሥት ጋር በመሆን የኢትዮጵያ ርስት የሆነውን ዴር ሡልጣንን ሊቀሙን የተለያየ ዘዴ እየተጠቀሙ ያሉትን ግብጻውያንን ለማስቆምና ቤተ ክርስቲያን የርስቷ ሕጋዊ ባለቤት ሆና እንድትዘልቅ መንግሥት ከቤተ ክርስቲያን ጎን እንዲቆም ሲያሳስቡ ኖረዋል፡፡

ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ገብርኤል (ዶ/ር)ወደ ሀገር ቤት ከተመለሱም በኋላ በተለያዩ ቦታዎች ተዘዋውረው ቤተ ክርስቲያንን አገልግለዋል። ዘርፈ ብዙ መንፈሳዊ አገልግሎት ከሰጡባቸው ቦታዎች ውስጥ የሲዳማ፣ጌዴኦ አማሮና ቡርጂ ዞን ሀገረ ስብከት አንዱ ነው። ከኅዳር ወር ፳፻፫ ዓ.ም ጀምሮ በቅዱስ ሲኖዶስ መልካም ፈቃድ በጸሎትና በቡራኬ እንዲቆዩ እስከተወሰነበት እስከ ጥቅምት ፳፻፲፫ ዓ.ም ድረስ በርካታ ሐዋርያዊ አገልግሎትን በሀገረ ስብከቱ ላይ አከናውነዋል። በሀገረ ስብከቱ የሚነገሩ የሲዳምኛ፣ጌዴኦኛ፣ ኮሬ እና ቡርጂኛ ማስተማር የሚችሉ ካህናትን እና ሰባክያንን ወንጌል በማሠልጠን እንዲሁም በማሰማራት ስብከተ ወንጌል እንዲስፋፋ አድርገዋል። በዚህ መንፈሳዊ እንቅስቃሴም ከ፶ ሺህ በላይ አዳዲስ አማንያንን ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ ከማኅፀነ ዮርዳኖስ ተወልደው ልጅነትን እንዲያገኙ አድርገዋል። በሐዋርያዊ ጉዞም ምእመናንን በዕለታዊ የስብከተ ወንጌል መርሐ ግብራት ከመሳተፍ ጀምሮ በክብረ በዓላት እንዲሁም የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች በሚያጋጥሙበት ወቅትም ጭምር ችግሩ በተከሠተበት አካባቢ በአካል በመገኘት ምእመናንን ሲያስተምሩ እና ሲያጽናኑ ቆይተዋል።

ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ገብርኤል (ዶ/ር)አብያተ ክርስቲያናት ባልተተከሉባቸው አካባቢዎች የስብከተ ወንጌል ኬላዎች እንዲከፈቱ በማድረግ ትምህርተ ወንጌል እንዲሰጥ አድርገዋል። በዚህ ረገድ ከማኅበረ ቅዱሳን ጋር በመሆን በሀገረ ስብከቱ የሚያከናውኑ የስብከተ ወንጌል አገልግሎቶችን በማስፋፋት እንቅስቃሴዎች ውጤታማ እንዲሆኑ አድርገዋል። የሐዋሳ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ገብርኤል ገዳምም ዕውቅና እንዲያገኝና በደብዳቤ እንዲጸድቅ አድርገዋል። ወንዶ ገነት ደብረ ገነት ቅድስት ኪዳነ ምሕረት አንድነት ገዳምም እንዲሁ ዓመታዊ የበጀት ድጋፍ እንድታገኝ ክትትል በማድረጋቸው ገዳማዊ ሥርዐት እንዲጠናከር አድርገዋል። ለሐዋሳ ደብረ መንክራት ቅዱስ ሚካኤል ወቅዱስ ተክለ ሃይማኖት አንድነት ገዳም ደግሞ በድጋፍ መልክ በጀት በመስጠት ገዳሙ የአብነት ትምህርት ማዕከል እንዲሆን በማድረግ አገልጋዮችና መምህራንን እንዲያፈራ አስችለዋል።

ከዚህ ቀደም ተሠርተው በአዲስ መልኩ ከታነፁት በርካታ አብያተ ክርስቲያናት በተጨማሪ ፵፰ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት እንዲታነጹ አድርገዋል። ገዳማትና አድባራት ገቢ ማስገኛ ሕንፃዎችን እንዲያንጹ፣ የተለያዩ ዝርያ ያላቸውን ዕጽዋት በየጊዜው እንዲተክሉ እንዲሁም ዳቦ ቤት፣ ከብት ርባታ፣ ትምህርት ቤት እና የመሳሰሉት የልማት ተቋማት እንዲሠሩ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል።

ብፁዕነታቸው ቤተ ክርስቲያን በዘመነ መንገድ ተደራጅታ ራስዋን እንድትችልና ከልመና እንድትወጣ በዘመናቸው ሲሠሩ ኖረዋል። ከልጅነት የአብነት ትምህርት ቤት ሕይወታቸው ጀምሮ ከዚህ ዓለም ድካም እስካረፉበት ጊዜ ድረስ ብዙ ፈተናዎችን በትዕግሥት በማለፍ ለቤተ ክርስቲያን ሲሠሩ ኖረዋል። በተለይ የሲዳማ፣ጌዴኦ አማሮና ቡርጂ ዞን ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ሆነው ሲያገለግሉ በቁጥር አነስተኛ የሆነው የሀገረ ስብከቱ ምእመን በሌሎች እምነት ተከታዮች የሚደርስበትን ጫናና ፈተና አብረው በመካፈል በዚህ ረገድ በጎ ሥራዎችን ሠርተዋል። ከመንግሥትም ሆነ ከሌሎች ቤተ እምነቶች የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመፍታት፣ ምእመናንንም በማጽናናት እንዲሁም የፈረሱ እና የተቃጠሉ አብያተ ክርስቲያናትን እንደገና አሳንፀዋል። በተለይ በሀገረ ስብከቱ ላይ የፕሮቴስታንታዊ ተሐድሶ እንቅስቃሴ መሠረቱን ጥሎ ለመስፋፋት ጥረት ሲያደርግ በነበረበት ወቅት ወደ ጥፋት መንገድ እየተጓዙ የነበሩ እኅቶችና ወንድሞችን በጸሎትና በትምህርት እንዲመለሱ አድርገዋል። በስሕተታቸው ጸንተው የሚገኙትና በምክር መመለስ አሻፈረኝ ያሉትን ግለሰቦች ተገቢ መረጃዎችን ለቅዱስ ሲኖዶስ በማቅረብ ከምእመናን አንድነት እንዲለዩ ከማድረግ ባሻገር እንዲህ አይነቱን ሁኔታ በዘላቂነት ለመከላከል የተጠናከረ የስብከተ ወንጌል አገልግሎትን ሲያስፋፉ ቆይተዋል።

ብፁዕነታቸው በሀገር ውስጥ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ቤተ ክርስቲያን የሰጠቻቸውን መንፈሳዊ አገልግሎት በትጋት ከመወጣት ባሻገር ከሌሎች አኃት አብያተ ክርስቲያናት ጋር የጠበቀ ግኑኝነት እንዲኖራት ብዙ ሠርተዋል።

ለምሳሌ በኦሪየንታል ኦርቶዶክስ አብያት ክርስቲያናትና በምሥራቅ ኦርቶዶክስ መካከል በነበረው የነገረ መለኮት ውይይት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን በመወከል በርካታ ውይይቶችን ተሳትፈዋል፡፡ በደርግ ዘመንም ሁለተኛው ቅዱስ ፓትርያርክ በግፍ በመገደላቸው ምክንያት ተቋርጦ የነበረው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እና የእስክንድርያ ኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ግንኙነት እንደገና እንዲጀመር፣ በሌሎች ኦሪየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መካከል የነበረው ግንኙነትም ይበልጥ እንዲጠናከር ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡

በኦሪንታል ኦርቶዶክስና እና በሮም ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በቪየና ሲደረግ የነበረውን ይፋዊ ያልሆነ የነገረ መለኮት ውይይትና የኦሪየንታል አብያተ ክርስቲያናት ከአንግሊካን ቤተ ክርስቲያን ጋር በነበረው ውይይት የዓለም አቀፉ የነገረ መለኮት ጉባኤ አባል በመሆን አገልግለዋል፡፡ በአውሮፓውያን አቆጣጠር ፳፻፲፫ በእኛ በጥቅምት ወር ፳፻፮ ዓ.ም ደቡብ ኮርያ ቡሳን ላይ በተካሔደው በዐሥረኛው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት አጠቃላይ ጉባኤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ልዑካን በመምራት የጠቅላላ ጉባኤው አባል በመሆን ተሳትፈዋል፡፡

የኢትዮጵያ የሃይማኖት ጉባኤ በመመሥረት እንዲሁም ለተከታታይ ስድስት ዓመታት ያህል የጉባኤው የቦርድ ሰብሳቢና የካውንስል ጉባኤው ሰብሳቢ በመሆን ከሐዋሳ አዲስ አበባ ድረስ እየተመላለሱ ቤተ ክርስቲያን የሰጠቻቸውን ኃፊነት በብቃት በመወጣት ያለመሰልቸት አገልግለዋል፡፡ በአንዳንዶች ዘንድ ‹‹ ለውጥ ፈላጊ ጳጳስ ›› የሚል ስያሜ የተሰጣቸው ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ገብርኤል (ዶ/ር)በቤተ ክህነቱ ውስጥ የሰፈነውን ደካማና ኋላ ቀር አስተዳደር እንዲሻሻል ይፈልጉ እንደነበር ከሥራዎቻቸው ባሻገር በየጊዜው የሚጽፏቸው መጣጥፎች ምሥክሮች ናቸው፡፡ በተለያዩ በመገናኛ ብዙኃን ላይ በቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ ጉዳይ ላይ የሚያዩትን ክፍተቶች እርምት እንዲሰጥባቸው፣ ምእመናንም ሊያውቋቸው ይገባል ያሏቸውን ሞጋች የኾኑ ሐሳቦችን በማንሣት በበርካታ ጋዜጦችና መጽሔቶች ላይ ጽፈዋል፤ ሞግተዋል፤ አባታዊ አበርክቶአቸውን አስነብበውናል፡፡ ለምሳሌ ሊቃነ ጳጳሳት በቤተ ክርስቲያን አስተዳደር፣ ሰላም ይስፈን፤ በቤተ ክህነት ባለሥልጣናትና ከሥራ በተወገዱ ሊቃውንት መካከል የተፈጠረው የከረረ ጸብ በዕርቅ ይፈታ፤ የገንዘብ ምዝበራው ይቁም፤ ቤተ ክርስቲያን በሕገ ሐዋርያት በሲኖዶስ ትመራ፤ በየጋዜጣው የሚጻፈው የዘለፋና የነውር ደብዳቤ በዕርቅ ይቁም… ከጻፏቸው መጣጥፍ ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ገብርኤል (ዶ/ር)በቋንቋ ደረጃ ከሀገራቸው ቋንቋዎች በተጨማሪ የእንግሊዝኛ፣ ቤሎሩስ፣ ሁለት የሩሲያ ዲያሌክት፣ የግሪክ ቋንቋዎችን በብቃት የሚናገሩ ሲሆን አርመንያን ቋንቋ በመጠኑ የሚናገሩ፣ ዓለም አቀፍ ሰብዕና የነበራቸው፣ መጻሕፍትን ማንበብና መመርመር የሚያስደስታቸው ታላቅ ምሁርና አባት ነበሩ፡፡ ብፁዕነታቸው ባደረባቸው ሕመም ምክንያት በጸሎት፣ በጸበልና በሕክምና ሲረዱ ቆይተው በተወለዱ በ፸ ዓመታቸው ኅዳር ፳፯ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም ከዚህ ዓለም ወደማያልፈው ዓለም ከሞት ወደ ሕይወት ከድካም ወደ ዕረፍት ተሻግረዋል፡፡

የተከበረ አስከሬናቸውም በዕለቱ ከቀኑ ዐሥር ሰዓት ላይ ወደ መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ተወስዶ ጸሎተ ፍትሐት ሲደረስበትና ሲቀደስበት ካደረ በኋላ ሥርዓተ ቀብራቸው ፦
ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት

ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት ወኤጲስ ቆጶሳት የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት
የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት የየመሪያውና የየድርጅቱ ኃላፊዎች

የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሠራተኖች የሥራ ኃላፊዎች አድባራትና ገዳማት አስተዳዳሪዎች

እንዲሁም የመንፈስ ቅዱስ ልጆቻቸው ወዳጅ ዘመዶቻቸው በተገኙበት

*ኅዳር ፳፯ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም ከጠዋቱ በ፬፡ሰዓት በአዲስ አበባ መንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ተፈጽሟል፡፡*

# “መንፈሳዊ የቱሪስት መዳረሻዎች የትውልዱን ሞራል ከመገንባት ባሻገር መንፈሳዊ ርካታን የሚሰጡ ናቸው”

*- ፈለገ ጥበብ ደ/ር አለማየሁ ዋሴ (የእመጓ መጽሐፍ ድራሲ)*



ፈለገ ጥበብ ደ/ር አለማየሁ ዋሴ

*በካሣሁን ለምለሙ*

*ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ የቱሪስት መስህቦች ውስጥ አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱሳት መካናትና የአደባባይ በዓላቷ ናቸው። በዚህም ሀገርና መንግሥት ተጠቃሚዎች ናቸው። በተለይ መንግሥት ከቱሪዝም ዘርፍ የሚያገኘው ገቢ ቀላል አይደለም። ነገር ግን በአብዛኛው የገቢ ምንጭ የሆኑትን ዘመን የጣላቸውንና ጊዜ የረሳቸውን ገዳማትና አድባራት በገቢ ራሳቸውን እንዲችሉ፤ ከጊዜ ብዛት የፈረሱና የተጎሳቆሉት ደግሞ እንዲጠገኑ የማድረግ ተግባር ውስጥ ሲገባ አይስተዋልም። ለከተሞችና ለገጠር ቀበሌዎች የመሠረተ ልማት ዝርጋታ በሚደረግበት ጊዜ እንኳ ገዳማትና የአብነት ትምህርት ቤቶችን ያገለለ እንደሆነ በማኅበረ ቅዱሳን የቅዱሳት መካናትና መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶች አገልግሎት ማስተባበሪያ ም/ኃላፊ በቅርቡ ባሕር ዳር በተዘጋጀ መርሐ ግብር ላይ ካቀረቡት ሪፖርት ማርጋገጥ ተችሏል። ለምሳሌ በቅርቡ በተከሰተው የኮሮና ቫይረስ ወቅት በሽታውን ለመከላከል የሚያስፈለጉ ግባአቶችንና ሕክምናዎችን የአብነት ተማሪዎች ማግኘት አልቻሉም። የአብነት ተማሪዎች የሀገሪቱ ዜጋ አንድ አካል ሆነው ሳለ በመንግሥት ከሚቀርቡ ድጋፎችና ማኅበራዊ አግልግሎቶች ውጭ ሲደረጉ ቆይተዋል።*

*ለገዳማቱና አድባራቱ አስፈላጊ የሆኑ መሠረተ ልማቶችን ሳያሟሉ ከቱሪዝም ሀብት የሚገኘውን ገቢ ብቻ መሰብሰብ መንግሥትንና ሀገርን ውጤታማ አያደርግም። መንግሥት ለቤተ ክርስቲያን እያደረገ ያለው ድጋፍ አናሳ ወይም ጭራሽ የሌለ መሆኑን የተረዳችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የገንዘብ አቅም ካላት በራሷ ከሌላት ደግሞ ልጆቿን አስተባብራ በጊዜ ብዛት የወደቁ ገዳማትን ጠግና የዕለት ቀለብ የሌላቸውን ደግሞ የዕለት ቀለብ ሰፍራ ገዳማዊ ሕይወት እንዲመሩ አድርጋለች። ከከተማ የራቁ ገዳማትና አድባራት አቅም በፈቀደ ሁሉ የመሠረተ ልማት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ስትሠራ ቆይታለች።*

*ቤተ ክርስቲያን ከምታደርገው ድጋፍ ውጭ አንዳንድ ግለሰቦች አድባራትንና ገዳማትን በራሳቸው ተነሳሽነት በመደገፍ ክርስቲያናዊ ግዴታቸውን ሲወጡ ይስተዋላል። አድባራትን የሚሠሩ፣ የዘመመውን የሚያቀኑ፣የዕለት ቀለብ ለሌላቸው ገዳማት የዕለት ቀለብ የሚሰፍሩ እንዲሁም የአብነት ትምህርት ቤቶችን በገንዘብ፣ በጉልበትና በአሳብ*

***የሚያግዙ ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያኖች በርካቶች ናቸው፡፡ ከእነዚህ ግለሰቦችና በጎ አድራጊ ምእመናን መካከል ፈለገ ጥበብ ዶ/ር አለማየሁ ዋሴ በምሳሌነት ይጠቀሳሉ፡፡ ፈለገ ጥበብ ዶ/ር አለማየሁ ዋሴ "እመጓ" የተባለችውን የመጀመሪያ መጽሐፋቸውን ለማኅበረ ቅዱሳን በስጦታ በማበርከት ከመጽሐፉ ሽያጭ የሚገኘው ገቢ ለተለያዩ ገዳማት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ እንዲውል አድርገዋል፡፡ ከዚህ መጽሐፍ ሽያጭ ከተገኘው ከ ፩.፰ ሚሊዮን ብር በላይ ለሰባት ገዳማት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ውሏል፡፡ እነዚህ ሰባት ፕሮጀክቶች መጠናቀቃቸውን አስመልክቶ በባሕር ዳር ዩኒሰን ሆቴል ባዘጋጀው መርሐ ግብር ላይ መልእክት ካስተላለፉት ፈለገ ጥበብ ዶ/ር አለማየሁ ዋሴ ጋር በዕለቱ ዝግጅት ክፍላችን አጭር ቆይታ አድርጓል፡፡ ያደረግነውን ቆይታም እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡ መልካም ንባብ፡፡***

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** ገዳማት በገቢ ራሳቸውን እንዲችሉ ምን መሠራት አለበት ይላሉ?

***ፈለገ ጥበብ ዶ/ር አለማየሁ ዋሴ፡-*** አንዳንዴ በሀገራችን ኢትዮጵያ የሚስተዋለው ችግር የቱሪዝም ሀብቷን አሟጦ አለመጠቀሟ ነው፡፡ አብዛኛው የቱሪስት መዳረሻዎች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሀብቶች ናቸው፡፡ እነዚህ መንፈሳዊ የቱሪስት መዳረሻዎች የትውልዱን ሞራል ከመገንባት ባሻገር መንፈሳዊ ርካታን የሚሰጡም ናቸው፡፡ እነዚህን ቦታዎች በማስጎብኘት የአካባቢው ኅብረተሰብ ኢኮኖሚ እንዲነቃቃ ማድረግ ይቻላል፡፡ በተለይ በዚህ መንገድ የገዳማትንና አድባራትን ገቢ በመጨመር ራሳቸውን የሚችሉበትን መንገድ ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡

ሰው አንድን መንፈሳዊ ቅርስ ለመጎብኘት ሲሄድ ከሚያገኘው መንፈሳዊ ርካታ ውጭ ለአካባቢው ኅብረተሰብ የኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ ኢትዮጵያ ከሌላው ሴክተር ከምታገኘው ገቢ በበለጠ ከመንፈሳዊ ቅርሶች የሚገኘው ገቢ ይበልጣል፡፡ ስለሆነም ከምንጊዜውም በላይ የበለጠ ገቢን ለመሰብሰብ ገዳማቱንና አድባራቱን መንከባከብ፣ ማደስና ራቸውን በገቢ እንዲችሉ የማድርግ ሥራ ተጠናክሮ መሠራት አለበት፡፡ ይህ ሥራ ደግሞ የመንግሥት፣ የቤተ ክርስቲያንና የሁሉም የሀገሪቱ ዜጋ ድርሻ ሊሆን ይገባል፡፡ እኔም ባለኝ አቅም የድርሻዬን መወጣት ስለነበረብኝ በጥሬ ገንዘብ ድጋፍ የማድረግ አቅሙ ባይኖረኝም የአእምሮዬ ውጤት የሆነውን መጽሐፌን (እመጓን) ለአድባራትና ገዳማት ማጠናከሪያ እንዲሆን ሰጥቻለሁ፡፡ የመጀመሪያ ሥራዬ የሆነውን ‹‹እመጓ›› መጽሐፍ ለማኅበረ ቅዱሳን በመስጠት ማኅበሩም ከ፩ ሚሊዮን ብር በላይ በመሸጥ ለሰባት አድባራትና ገዳማት ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ አውሎታል፡፡ ይህ ከመጽሐፉ ሽያጭ የተገኘው ከ፩ ሚሊዮን ብር በላይ ገንዘብ ገዳማቱን በዚህ ደረጃ መደገፍ ከቻለ ሁሉም የድርሻውን ቢወጣ መንፈሳዊ ቅርሶቻችን ተጠብቀው ከትውልድ ወደ ትውልድ ይተላለፋሉ ማለት ነው፡፡

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** ከመጽሐፉ ሽያጭ የተገኘው ገቢ ለሰባት ገዳማት ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ መዋሉ ይታወቃልና በቀጣይስ ከርስዎ ምን እንጠብቅ?

***ፈለገ ጥበብ ዶ/ር አለማየሁ ዋሴ፡-*** መጽሐፉ ዘመን ተሻጋሪ ነው፡፡ ስለሆነም የመጽሐፉ ሽያጭ ይቀጥላል፡፡ ከመጽሐፉ የሚገኘው ገቢም ለሌሎች ገዳማት ፕሮጀክቶች ማጠናከሪያ ይውላል፡፡ ከዚህ ቀደም ከመጽሐፉ ሽያጭ ከተገኘው ገቢ ተጠቃሚ የሆኑ ሰባቱ ገዳማት ሙሉ በሙሉ ችግሮቻቸው ተፈትተዋል ማለት ባይቻልም ግን ተቃሏል ማለት ይቻላል፡፡ ከእነዚህ ውጭ የሆኑ ሌሎች በችግር ውስጥ ያሉ ገዳማትን የተለያየ የገንዘብ ምንጭ እየፈለኩ መርዳት እፈልጋለሁ፡፡ ገዳማቱ በችግር ምክንያት ከሚሰጡት መንፈሳዊ አገልግሎት ሊገቱ አይገባምና፡፡ እንደ እኔ አሳብ በጣም ችግር ላይ የወደቁ ገዳማትን በመለየት ለመደገፍ እቅድ አለኝ፡፡ አንዳንድ ገዳማት ምግብ ሌሎች ደግሞ ትምህርት ቤት ወይም መጠለያ ሊያስፈልጋቸው ይችላል፡፡

ስለዚህ እነዚህን ሁሉ ችግሮች በተቻለ አቅም ቀስ በቀስ ሟሟላት ያስፈልጋል:: በመሆኑም ዕድሜዬና አቅሜ በፈቀደው ሁሉ ገዳማቱንና አድባራቱን የመደገፉ ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል:: ከዚህ በኋላ በጽሑፎቼ ገዳማትና አድባራትን ለመርዳት ጥረት አደርጋለሁ:: በየጊዜው የተሻለ ሥራ ለመሥራት ጥረት አደርጋለሁ:: ‹‹እመን›› በሚል ርዕስ የጻፍኩትን መጽሐፍ ለገዳማትና አድባራት መርጃ እንዲውል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከተችው ባለቤት ነች::

በቀጣይም ገዳማትን ለመርዳት ከቤተሰቤና ከባለቤቴ ጋር በመተባበር አቅሜ የፈቀደውን ሁሉ አደርጋለሁ:: የሥራዬን ውጤት በዛሬው ዕለት በማኅበረ ቅዱሳን በኩል በማየቴ እጅግ ተደስቻለሁ:: ገዳማቱ በእኔ የእጅ ሥራ መረዳታቸው ከፍተኛ ደስታ ሰጥቶኛል:: የሚገባኝን ያህል አደረኩ ባልልም ሌሎች ሰዎች ገዳማትንና አድባራትን ለመርዳት ምክንያት መሆኔ ያኮራኛል:: ለቤተ ክርስቲያን የግድ ገንዘብ ቆጥሮ መስጠት ላይቻል ይችላል ነገር ግን ባለን መክሊት ሁሉ መረዳት እንችላለን::

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** ገዳማውያኑ እንዳይበተኑ ገዳማቱም ወደ ፍርስራሽነት እንዳይለወጡ ከመንግሥትና ከማኅበረሰቡ ምን ይጠበቃል ይላሉ?

***ፌለገ ጥበብ ዶ/ር አለማየሁ ዋሴ፡-*** የቱሪዝም ሀብት የሀገርን ክፍለ ኢኮኖሚ ከሚያነቃቁ ነገሮች መካከል አንዱ ነው:: የቱሪዝም ሀብት ሲባል ደግሞ ካለን የተፈጥሮ ሀብት በተጨማሪ ባህላዊ ሃይማኖታዊ፣ አድባራት፣ ገዳማት፣ ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀሱ ቅርሶችን ያጠቃልላል:: እነዚህ እንዳይጠፉ መንከባከብ ብቻ ሳይሆን ለቱሪስት አመቺ ማድረግ አስፈላጊ ነው:: የቱሪዝሙ ተጠቃሚ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ባለመሆኗ ከመንግሥት በተጨማሪ ሁሉም ዜጋ የራሱን ድርሻ ሊወጣ ይገባል:: ሁሉም የአቅሙን ያህል ካደረገ ሲሰባሰብ ጥሩ ውጤት ያስገኛል::

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** ጠንካራ ትውልድን በጽሑፍ እንዴት መገንባት ይቻላል?

***ፌለገ ጥበብ ዶ/ር አለማየሁ ዋሴ፡-*** የቀደመውን ትውልድ ከአሁኑ ትውልድ ጋር ማነጻጸር ብዙ ባይጠቅምም የድሮውን ትውልድ ጥንካሬና የሞራል ልዕልና ከሁኑ ትውልድ ጋር ማስተሳሰር ያስፈልጋል:: የደከመውን ትውልድ ከነቃው ትውልድ ጋር ማስተባበር ያስፈልጋል:: ደካማውን በመተው ጠንካራውን ደግሞ በማስቀጠል ነው ትውልድ ሊገነባ የሚችለው:: ሀገራችን ኢትዮጵያ ብዙ ጸጋ ስላላት ጨለማውን ሳይሆን ብርሃኑን ማየት ብንችል ሀገራችን ጥሩ ተስፋ ይኖራታል:: ሀገርንና ትውልድን ለመቅረጽ ከምንጠቀምባቸው ነገሮች አንዱ ጽሑፍ ነው:: ጽሑፉ በተለያየ መንገድ ሊጻፍ ይችላል:: ለማስተማርና ለማዝናናት ሊሆን ይችላል:: ትውልድን ለመቅረጽ ግን አንድነትንና የሞራል ልእልናን ከፍ ሊያደርጉ የሚችሉ ጽሑፎች መጻፍ አለባቸው:: ይህ ሲሆን ጠንካራ ትወልድን መገንባት ይቻላል::

***ስምዐ ጽድቅ፡-*** በመጨርሻ ቀር የሚሉት ነገር ካል?

***ፌለገ ጥበብ ዶ/ር አለማየሁ ዋሴ፡-*** ሁላችንም የራሳችን አቅም አለን:: ያለን አቅማችን ተጠቅመንን ጃንጥላ ይዛ የምትለምነውን ቤተ ክርስቲያናችንን ከልመና ልናወጣት ይገባናል:: እኔ ምሳሌ የሆንኩት በርካታ ቤተ ክርስቲያንን በገንዘባቸው፣ በዕውቀታቸውና በሐሳባቸው የሚያግዙ እህትና ወንድሞችን ያመጣል ብዬ ስለማምን ነው:: ሀብታም ብቻ የሚሰጥ እንዳይመስለን፤ ደኀም ይሰጣል:: ነገር ግን ለመስጠት ለመርዳት መወሰንና ፍላጎት ማሳየትን ይጠይቃል:: ስለዚህ እኔ በሰጠሁት መጽሐፍ ሽያጭ የተገኘው ገቢ ለሰባት ገዳማት ፕሮጀክቶች ማጠናቀቂያ ሆኗል፤ የዚህ መጽሐፍ ሽያጭም እስካሁን ድረስ አልቆመም:: በመሆኑም ከዚህ ቀደም ከመጽሐፉ በተገኘው ገቢ የተረዱ ገዳማት እንዳሉ ሆኖ ምንም የሌላቸውና ችግር ላይ የወደቁ ገዳማት በመኖራቸው ከዚህ በኋላ የሚገኘው ገቢ በሙሉ ለእነዚህ ገደማት ጥቅም ይውላል::

# አስተርእዮ ማርያም

**በእህተ ሚካኤል**



የእግዚአብሔር ልጆች! እንደምን ከርማችኋል? በእግዚአብሔር ጥበቃ በሰላምና በጤና እንደቆያችሁን ተስፋ እናደርጋለን፤ በቤታችሁ ሆናችሁ ትምህርታችሁን በንቃት እየተከታተላችሁ ነው? በጣም ጎበዞች! በመንፈሳዊም በሥጋዊም ዕውቀት ማደግ ይኖርባችኋልና በርቱ!

ልጆች! ዛሬ የእመቤታችን በዓለ ዕረፍት ታሪክ ይዘንላችሁ ቀርበናልና ተከታተሉን!

ልጆች! በመጀመሪያ ‹‹አስተርእዮ›› ማለት መገለጥ ማለት ነው:: ‹‹አስተርእዮ›› ቃሉ ‹‹አስተርአየ ታየ፣ ተገለጠ›› ከሚለው የግዕዝ ግሥ የተገኘ ነው:: ልጆች! ጌታችን መድኃኒታችን ኢሱስ ክስቶስ በገባው ቃል ኪዳን መሠረት በሥጋ የተገለጠበት (የታየበት) አንድነት ሦስትነቱም የተገለጠበት ወቅት በመሆኑ ከልደት በዓል ጀምሮ እስከ ዐቢይ ጾም መግቢያ ዋዜማ ጊዜ ‹‹ዘመነ አስተርእዮ›› ይባላል::

የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም በዓለ ዕረፍት ጥር ፳፩ ስለሆነ እና በዘመነ አስተርእዮ ውስጥ ስለሚከበር ‹‹በዓሉ አስተርእዮ ማርያም›› ይባላል::

ልጆች! እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከአባቷ ከቅዱስ ኢያቄምና ከእናቷ ከቅድስት ሐና ከተወለደችበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዐረፈችበት ጊዜ ድረስ በምድር ላይ ፷፬ ዓመታትን ኖራለች:: እመቤታችን ከተወለደች በኋላ በእናት በአባቷ ቤት ፫ ዓመት፣ በቤተ መቅደስ ውስጥ ፲፪ ዓመት ፣በቤተ ዮሴፍ ፱ ወር ከልጅዋ ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ፴፫ ዓመት ከ፫ ወር እንዲሁም ከጌታ ዕርገት በኋላ ከወንጌላዊው ከቅዱስ ዮሐንስ ጋር ደግሞ ፲፭ ዓመት በድምሩ ፷፬ ዓመታትን በዚህ ዓለም ኖራ ጥር ፳፩ ቀን በ፵፱ ዓ.ም በክብር ዐርፋለች::

ልጆች! የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን ሞትና ትንሣኤ አባቶቻችን በጾመ ፍልሰታ ውዳሴ ማርያም ቅዳሴ ማርያም ሲተረጉሙ ዕረፍቷ በጥር ፳፩ በዕለተ እሑድ ነው:: እመቤታችን በዚህ ዓለም ፷፬ ዓመት ኖራ ጥር ፳፩ ቀን በዕለተ በእሑድ ጌታ እልፍ አእላፋት መላእክቱን አስከትሎ መጥቶ ‹‹እናቴ ሆይ ከዚህ ዓለም ድካም ላሳርፍሽ መጣሁ›› አላት::

እመቤታችንም ‹‹ልጄ ሰማይና ምድር የማይወስኑህ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በማሕጸኔ ተሸክሜ በድንግልና ወልጄህ እሞታለሁን?›› አለችው::

ጌታም በሲኦል የሚሠቃዩ ነፍሳትን አሳይቶ ‹‹እናቴ ሆይ ሞትሽ ለእነዚህ ቤዛ ይሆንላቸዋል›› አላት:: እመቤታችንም ‹‹እኒህን ከማርክልኝስ ይሁን›› አለችው:: ጌታም ቅዱስ ሥጋዋን ከቅድስት ነፍሷ ለይቶ በዝማሬ መላእክት ዐሳረጋት:: ደቀ መዛሙርቱንም ከያሉበት በደመና ጠቅሶ ካለችበት አድርሶ እመቤታችሁን ሥጋዋን በክብር ዐሳርፉ አላቸው::

ሐዋርያት በአጎበር አድርገው ወደ ጌቴሴማኒ ይዘው ሲሄዱ አይሁድ ቀድሞ ልጇን ተነሣ ዐረገ እያሉ ሲያውኩን ይኖራሉ አሁን ደግሞ እሷን ተነሣች ዐረገች እያሉ ሊያውኩን አይደለምን? በእሳት እናቃጥላታለን ብለው ተነሡ:: ታውፋንያ የሚባል አይሁዳዊም ተራምዶ የእመቤታችን አስከሬን ያለበትን አጎበር ጨበጠው:: በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ መጥቶ የታውፋንያን እጆች በሰይፍ ሰየፋቸው እጆቹም ከአጎበሩ ላይ ተንጠልጥለው ቀሩ:: ታውፋንያ በዚህ ጊዜ‹ ‹‹በእውነት የአምላክ እናት ናት›› በማለት ስለአመነ እጆቹ ተመለስው እንደነበሩ ሆኑለት::

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም የእናቱን የቅድስት ድንግል ማርያምን ሥጋ ተቀብሎ ከሐዋርያት ቅዱስ ዮሐንስን በማስከተል በደመና ነጥቆ ከገነት በማስገባት ከዕፀ ሕይወት ሥር አኖራት:: ቅዱስ ዮሐንስ ወደ እነሱ ሲመለስም ሐዋርያት ስለ እመቤታችን ጠየቁት እርሱም ‹‹ በገነት ከዕፀ ሕይወት ሥር አለች›› አላቸው:: ሐዋርያትም ቅዱስ ዮሐንስ አይቶ እኛ ሳናይ ብለው እመቤታችንን እንዲያሳያቸው በነሐሴ መጀመሪያ ጾም ጀመሩ ሁለት ሱባዔ (ከነሐሴ ፩ እስከ ፲፬) እንደጾሙ ጾሙ ሲፈጸምም እሑድ አምጥቶ የእመቤታችንን ሥጋ ሰጣቸው ሐዋርያትም በክብር ተቀብለው ቀበሯት::

እመቤታችንም በተቀበረች በሦስተኛው ቀን እንደ ልጇ ተነሥታለች:: እመቤታችን በተነሣች ጊዜ ቅዱስ ቶማስ አልነበረም በደመና ተጭኖ ከሚሰብክበት ሀገረ ስብከቱ ሲመጣ እመቤታችን ወደ ሰማይ ስታርግ አገኛት:: እሱም ‹‹ቀድሞ የልጅሽን ትንሣኤ ሳላይ ቀረሁ ዛሬ ደግሞ የአንችን ትንሣኤ ሳላይ ልቀርነውን?›› ብሎ ሲያዝን እመቤታችን ‹‹አይዞህ አትዘን እነርሱ ትንሣኤዬን ዕርገቴንም አላዩም አንተ ግን አይተሃልና ተነሣች ዐረገች ብለህ ንገራቸው›› ብላ የያዘችውን (የተገነዘችበትን) ሰበን ሰጥታ ላከችው::

ከዚህ በኋላ ሐዋርያው ቶማስ ወደ ሐዋርያት በመሄድ ‹‹የእመቤታችን ነገር እንደምን ሆነ? በማለት ጠየቃቸው:: እነርሱም አግኝተን ቀበርናት አሉት:: እርሱም ‹‹ሞት በጥር በነሐሴ መቃብር ተው ይህ ነገር አይመስለኝም›› አላቸው:: ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም አንተ ሁል ጊዜ ለምን ትጠራጠራለህ? ብሎ በመገሠጽ እመቤታችን የተቀበረችበትን ሊያሳየው ወደ መቃብሩ ይዞት ሄደ:: ከመቃብሩም ደርሰው ቢከፍተው እመቤታችንን አጣት በዚህን ጊዜ ደንግጦ ቆመ::

ሐዋርያው ቶማስም አታምኑኝም ብዬ ነው እንጂ እመቤታችንስ ተነሣች፤ ዐረገች አላቸው የያዘውንም ሰበን ሰጣቸው ሐዋርያትም ለበረከትም ተካፈሉት:: በዓመቱ ደግሞ ሐዋርያት ቅዱስ ቶማስ ትንሣኤሽን ዕርገትሽን አይቶ እኛ ሳናይ ብለው መጾም ጀመሩ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ጾምና ጸሎታችውን ተቀብሎ በ፲፮ኛው ቀን እመቤታችንን መንበር ቅዱስ ጴጥሮስን ተራዳኢ ካህን ቅዱስ እስጢፋኖስን ደግሞ ሠራዒ ዲያቆን አድርጎ በዚያው ላይ ቀድሶ አቄረባቸው:: ቤተ ክርስቲያንም ይህንን መታሰቢያ አድርጋ በዓለ ዕረፍቷን በየዓመቱ ታከብረዋለች::

ልጆች! እናንተም በጥር ፳፩ የአስተርእዮ ማርያም በዓል ከቤተ ሰቦቻችሁ ጋር ሆናችሁ እንዳከበራችሁ ተስፋ እናደርጋለን:: በሉ የዛሬን ትምህርት በዚሁ እንጨርሳለን፤ በደኅና ሰንብቱ!

*ከእመቤታችን ረድኤት፣ በረከት ያሳትፈን! አሜን::*

*ወስብሐት ለእግዚአብሔር*

# የቤተ ክርቲስያን አብያተ መጻሕፍት ነገር

ኪኑኪሩ ከአዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ጥንታዊም ሆነ ዘመናዊ ታሪኮች የሚጠኑት በአመዛኙ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ምንጭ እየተደረጉ ነው:: የሀገራችንም የባህል፣ የትምህርት፣ የማኅበራዊ እሴቶች ቤተ መዛግብት ሆና ስታገለግል የኖረችው ቤተ ክርስቲያን ነች:: ስለዚህ የሀገራችንና የውጪ ሀገር ሊቃውንት የጥናት ማእከል ቤተ ክርስቲያንና የቤተክርስቲያን ሀብቶች ናቸው:: በተለይ የቤተ ክርስቲያን የጽሑፍ ሀብቶች እጅግ ከፍተኛ ጥቅም ያላቸው ናቸው:: ቅርስ ከመሆናቸውም አልፎ ለጥናት ምርምር ዋነኛ የመጀመሪያ ደረጃ ምንጮች ናቸው::

እነዚህ መጻሕፍት በየገዳማቱና አድባራቱ ዕቃ ቤቶች በክብር ተቀምጠው እንደሚገኙ ይታወቃል፤ ሌሎች ደግሞ ከቀደሙ ዘመናት ጀምሮ በተለያዩ ምክንያቶች/በምርኮና በዝርፊያ/ ከሀገር ወጥተው የሌሎች ሀገራት ሙዚየሞችና አብያተ መጻሕፍት ማክበሪያ ሆነዋል:: ይህ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትና ደቀ መዛሙርት ሳይቀሩ ለምርምርና ጥናት የሚፈልጓቸውን መጻሕፍት በቀላሉ ማግኘት እንዳይችሉ አድርጓል:: በአንድ በኩል በየገዳማቱና አድባራቱ መጻሕፍት መቀመጣቸው የማይጎዳ ሆኖ ለጥናትና ምርምር ግን በቀላሉ የማይገኙ፣ የማይፈቀዱ ሆነው ይታያሉ:: በውጪ ሀገራት ያሉት የገንዘብና የውጪ ጉዞ ሂደት ለማይቀናቸው ተመራማሪዎች በቀላሉ የሚገኙ አይደሉም::

የዚህ ችግር ዋነኛ ምክንያት ግን ቤተ ክርስቲያን እንደ ሀብቷ ብዛትና በዚህ ረገድ እንዳላት የጎላ ስም የሚመጥን አንቱ የተባለ ቤተ መጻሕፍት በስሟ ማቋቋም አለመቻሏ ነው:: ቤተ ክርስቲያን አብያተ መጻሕፍት ቢኖሯትም በሚገባ ያልተደራጁ፣ የሚፈለገውን ያህል አቅርቦት የሌላቸው፣ በሥርዓት በመደበኛ ጊዜ አገልግሎት የማይሰጡ ሰዓቱን ጠብቀው የማይከፈቱና የማይዘጉ . . . ወዘተ በመሆናቸው አርኪ አይደሉም:: ስለዚህ ተመራጭ አይደሉም ፤ ብዙ አንባቢም የላቸውም:: ለምሳሌ በጠቅላይ ቤተ ክህነት የሚገኘው የተሻለ የሚባለው ቤተ መጻሕፍት እንኳን ከሚከፈትበት የሚዘጋበት ጊዜ ይበዛል፣ ያለው አቅርቦትም ከቤተ ክርስቲያን ብዙ ሀብት አንጻር ኢምንት የሆነ ሲሆን በቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት አንቱታን ካገኙ የመንግስት ቤተ መዛግብትና ቤተ መጻሕፍት አንጻርም ሲታይ በአግባቡ የተያዘ አይደለም::

ሌሎች በማኅበራትና በሰንበት ትምህርት ቤቶች የተከፈቱ አብያተ መጻሕፍትም በሚሰጡት አገልግሎት ምስጉን ቢሆኑም ባላቸው የመጻሕፍት አቅርቦት አንጻር አጥኚና ተመራማሪ የሚፈለገውን ያህል አጥጋቢ አይደሉም:: ቢያንስ አንዱ በአንድ መስክ ሌላው በሌላ መስክ/ዓይነት/ መጻሕፍትን በበቂ በመያዝ አማራጭ መሆን የሚችሉበትን ዕድል አላሰፉም:: የሚቋቋሙትም በመዋጮ መጻሕፍት በመሆኑ እንደ ‹‹የኔ ቢጤ እህል›› በቂ ባልሆነ መጠን ደግሞም እጅግ በጣም የተደበላለቀ የመጻሕፍት ዓይነት በመያዝ ስለሚደራጁ የሚፈልጉትን አግኝቶ ለማንበብ ዕድል ይጠይቃል:: በዘመናዊ በካታሎግ አደረጃጀትም በቅደም ተከተል ሥርዓት አልተቀመጡም::

የትኞቹ አብያተ መጻሕፍት ገድላትን በመጻሕፍት፣ በቅጂ፣ በማይክሮፊል አሟልተው በመያዝ የገድል አጥኚዎችን ያስደስታሉ? የትኞቹ በነገረ ሃይማኖት /ዶግማ/ መጻሕፍት የተደራጁ ሆነው በዓይነት እነሱን በብርቱ ለሚፈልግ አንባቢ የሚጠቁሙ አብያተ መጻሕፍት ሆነዋል? ስንቶቹስ በታሪክ፣ በቋንቋ፣ በቀኖና ወዘተ ጉዳዮች ልዩ ቤተ መጻሕፍት ሆነው በመደራጀት ከሩቅም ከቅርብም አንባቢን ይጠራሉ? በዚህ ረገድ ያለንበት ደረጃ ዝቅተኛ ለመሆኑ በዓላማ በተለይም በጥናትና ምርምር መስክ ሥራዬ ብሎ ለመስማራት በሚሞክሩ ሰዎች በቀላሉ ለማግኘት ይረዳል፡፡

ቤተ ክርስቲያን አብያተ መጻሕፍትን በስፋት ማደራጀት የሚኖርባት የምእመናንን ሕይወትበቃለ መጻሕፍት ለማነጽ ነው፡፡ ይህ ማድረግ የሚቻለው ደግሞ የቤተ ክርስቲያን የሆኑ በቂ የጽሑፍ እና የሰነድ አቅርቦት ያላቸው አብያተ መጻሕፍት ሲደራጁ ነው፡፡ ተመራማሪዎችም በቂ ማስረጃ ባገኙ መጠን ቤተ ክርስቲያንን በበቂ የሚገልጥ የጥናትና ምርምር ውጤት ይኖራቸዋል፡፡ ከማስተዋወቅ ባለፈም የአገልጋዮችን አቅም በበቂ ይገነባል፡፡ በግርድፍ ዕውቀት አገልጋይ ሆኖ ከመሰለፍ ደቀ መዛሙርትን ያንጻል፡፡ ያላወቅናቸው ያልተረዳናቸውን ቤተ ክርስቲያዊ ጉዳዮች በጥናትና ምርምር በስፋትና በብቃት እንድናውቃቸው ያደርጋሉ፡፡ በተጨማሪም የማኅበራዊ አገልግሎትን ከመስጠት አንጻርም ለሀገርና ለመንግሥት በመስኩ የንባብ ማእከላትን በማስፋት ምስጉን ተብለው ከሚጠሩት ተቋማት አንዱና ዋነኛ መሆን ያስችላል፡፡ በተጨማሪም አብያተ መጻሕፍት ገቢ ማስገኛ እና ለአእምሮ ማሳረፊያ ሆነው ያገለግላሉ፡፡

የቤተ ክርስቲያን አብያተ መጻሕፍት በበቂ ሊደራጁ የሚችሉበት ሰፊ ዕድል አለ፡፡ በመላው ሀገሪቱ በሚገኙ አጥቢያዎች ያሉ ለጥናትና ምርምር የሚረዱ መጻሕፍትና ሰነዶችን በቅጂ በማግኘት ሀገራዊ ሀብት ማሰባሰብ ይቻላል፡፡ ምእመናን መጻሕፍትን በድጋፍና ትብብር እንዲሰጡ ቢጠየቅ በግዢና በስጦታ በርካታ መጻሕፍትን በአጭር ጊዜ ማግኘት ይቻላል፡፡

የተወሰነ በጀት መድቦ ደግሞ በሌላ አማራጭ ያልቀረቡና አዳዲስ የሆኑ መጻሕፍትን በመግዛት ማሟላት ይቻላል፡፡

ይህ ባለመሆኑ ግን የሀገሪቱ የመጻሕፍት ዋነኛዋ ባለሀብት ቤተ ክርስቲያን በደረጃ አነስተኛ የሆኑ አብያተ መጻሕፍት ቢኖሯትም አንድ እንኳን ስም ያለው፣ ግዙፍ፣ በሥርዓት እና ዘመናዊ በሆነ መንገድ የሚሠራ ቤተ መጻሕፍት ሊኖራት አልቻለም፡፡

ይህ ደግሞ የመጻሕፍት እናት ለሆነችው ቤተ ክርስቲያን ባለቤትነቷን ያሳጣታል፡፡ ስለዚህ በነበሩት ላይ አስፍቶ ማደራጀት ካልሆነም በአንድ ግዙፍ ፕሮጄክት ይህን ሐሳብ እውን የሚያደርጉ ሰዎችን እንዲያነሣ ወደ እግዚአብሔር መጸለይና የራስንም ጥረት ማድረግ ይገባል እንላለን፡፡

# ጥቅም ፍለጋ የገባሁበት ትዳር መውጫ አሳጥቶኛል

ውድ የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ አዘጋጆች እንደምን ሰነበታችሁ ስሜ ወለተ ገብርኤል ይባላል የምኖረው አሜሪካን ሀገር ሲሆን እድሜዬ ወጣት ከሚባሉት ውስጥ ነው፡፡ በዓለማዊ ትምህርት ሁለተኛ ዲግሪ አለኝ በልጅነቴ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አድጌያለሁ ያቺ እርሾ ናት ወደ እናንተ እንድጽፍ ያነሳሳችኝ፡፡ ወደ አሜሪካን ሀገር የሔድኩት ዲቪ የደረሰው የድሮ የትምህርት ቤት የክፍል ጓደኛዬን አግብቼ ነው፡፡ ያገባሁት አሜሪካን ሀገር ለመሄድ እንጂ የምወደው እና ትዳር መስርቼ አብሬው ለመኖር የምፈልገው የምወደው ሌላ የልጅነት ጓደኛ አለኝ፡፡ ያገባሁት ከዚህ ሀገር እንድወጣ ብቻ እንደሆነ ልቤ ቢያውቅም በተቃራኒው አግብቶ የወሰደኝ የክፍል ጓደኛዬ ግን ዛሬም ድረስ የእውነት ጋብቻ ከኔ ጋር እንደፈጸመ ነው የሚያውቀው፡፡ እሱን ፈትቼው ፍቅረኛዬን አግብቼ ወደ አሜሪካን ሀገር ለመውሰድ እቅድ አለኝ ይህንንም ከፍቅረኛዬ ጋር ቤተ ክርስቲያን በመሄድ እንደማልከዳው ነገሮች ሲመቻቹ ልጁን ፈትቼ እሱን በማግባት እንደምወስደው ቃል ገብቻለሁና ነው፡፡ ውድ የስምዐ ጽድቅ አዘጋጆች አሁን እያስጨነቀኝ ያለው እንደ እውነተኛ ሚስቱ የሚያስበኝ የአሜሪካው ባለቤቴ እንድወልድ ይፈልጋል እኔ ደግሞ ገና የማገባውና የምጠብቀው ሰው ስላለ ይህንን መፈፀም አልችልም፡፡ እውነቱን ነግሬው ለመለያየት እጅግ ተቸግሬአለሁ፡፡ ምክንያት ፈልጌ ልጣላው ሁሉ ብዙ ሞከርኩ ነገር ግን ለማደርግበት ክፉ ነገር ሁሉ ይቅርታ እያደረገ ያልፈኛል፡፡ ኢትዮጵያ ያለው ፍቅረኛዬ ደግሞ የፍቺዬን ቀን በጉጉት እየጠበቀ ነው፡፡ የኔም አካል አሜሪካን ይሁን እንጂ ልቤ ኢትዮጵያ ካለው ፍቅረኛዬ ጋር ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ፍርሃቴ ጨምሮ ቤተ ክርስቲያን መሄድ፣ መጸለይ ሁሉ አቁሜያለሁ፡፡ ጥቅም ፍለጋ እንደ ቀልድ የገባሁበት ነገር መውጫ አሳጥቶ እንቅልፍ ነስቶኛልና ከዚህ ጭንቀት እንዴት ልውጣ? እባካችሁ ከጭንቀቴ የምገላገልበትን መንገድ ጠቁሙኝ፡፡

ወለተ ገብርኤል በቅድሚያ ከጭንቀቴ የምገላገልበትን መንገድ ጠቁሙኝ ‹‹ጥቅም ፍለጋ የገባሁበት ትዳር መውጫ አሳጥቶኛል›› ብለሽ ላቀረብሽልን ጥያቄ እናመሰግናለን፡፡ ይህንን ጥያቄም ልታቀርቢ የቻልሽው አንቺው እንደ ገለጽሽው ዕድገትሽ ወቅት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመሆኑ ክርስቲያን የሆነ ሰው ሁሉ ለችግሩ መፍትሔ የሚያገኘው ከቤተ ክርስቲያን መሆኑን ኅሊናሽ ስላመነ ነው፡፡

ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በትምህርቱ እንደገለጸው ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ሐኪም ቤት ናትና፡፡ ለችግሮች ሁሉ መልስ አላት፡፡ ወለተ ገብርኤል ጋብቻን ጥንት ጥዋት የመሠረተ እግዚአብሔር መሆኑን በቅድሚያ ማመን ይገባሻል፡፡ ለአንድ አዳም አንዲት ሔዋንን ፈጥሮ ጋብቻን የመሠረተ እርሱ ነውና፡፡ በጥንተ ጠላት በዲያብሎስ ምክር ይህ ጋብቻን የመሠረተ እርሱ ነውና፡፡ በጥንተ ጠላት በዲያብሎስ ምክር ይህ ጋብቻ ቢፈርስም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአካለ ሥጋ በቃና ዘገሊላ በዶኪማስ ቤት ተገኝቶ የፈረሰውን ጋብቻ ባርኮና ቀድሶ ዳግም መሥርቷል፡፡

ወለተ ገብርኤል በዓለማዊ ትምህርትም ሁለተኛ ድግሪ አለኝ በልጅነቴም እድገቴ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው ብለሽናል፡፡ የመማር ጥቅሙ ለማወቅ፤ ያወቁትን ለመተግበር ነው፡፡ በልጅነትሽ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስታድጊ ስለጋብቻ ያለሽ ግንዛቤ የተሳሳተ ነበር ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ለአንድ አዳም አንዲት ሔዋንን የፈጠረ እግዚአብሔር መሆኑን አላስተዋልሽምና፡፡

ወለተ ገብርኤል ወደ አሜሪካ የሄድሽው አንቺው እንደገለጽሽልን ጥቅም ፍለጋ እንጂ እውነተኛ ትዳር መሥርተሽ አይደለም ይህንንም ልብሽ እያወቀ በማድረግሽ አሁን አብረሽው ያለሽው የትዳር አጋርሽን ዋሽተሽዋል፡፡ በነቢየ ልዑል ኢሳይያስ አድሮ እግዚአብሔር እንዲህ

ማለቱን ልብ በዪ። ‹‹ጌታም። ይህ ሕዝብ በአፉ ወደ እኔ ይቀርባልና በከንፈሮቹም ያከብረኛልና ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነውና በሰዎች ሥርዓትና ትምህርት ብቻ ይፈራኛልና›› (ኢሳ.፳፱፥፲፫)። በሰዎች ሥርዓትና ትምህርት ብቻ እግዚአብሔርን መፍራት ለእንዲህ ዓይነት ፈተና ይዳርጋል።

ወለተ ገብርኤል ከሁሉም በላይ መረዳት ያለብሽ ዐቢይ ጉዳይ ደግሞ የሚከተለው ነው። ‹‹መፋታትን እጠላለሁ ይላል የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር›› (ሚል.፪፥፲፮) እንግዲህ ወለተ ገብርኤል እግዚአብሔር አምላክ መፋታትን እጠላለሁ ካለ እግዚአብሔር የጠላውን የሚወድ ደግሞ ጥንተ ጠላት ዲያብሎስ መሆኑን ልትገነዘቢ ይገባል። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም አይሁድን ሲገሥጽ ያስተማረውን ቃል አስተውይ። ቃሉም እንዲህ ይላል። ‹‹እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ። የአባታችሁንም ምኞች ልታደርጉ ትወዳላችሁ እርሱ ከመጀመሪያ ነፍስ ገዳይ ነበረ እውነትም በእርሱ ስለሌለ በእውነት አልቆመም ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል ሐሰተኛ የሐስትም አባት ነውና። ››( ዮሐ.፰፥፵፬)

ወለተ ገብርኤል በቅድሚያ የሐሰት መገኛ ምንጩ ዲያብሎስ መሆኑን በጌታችን ትምህርት መረዳት ከቻልን አንቺ በቅድሚያ ወደ ሀገረ አሜሪካ ለመሄድ ብለሽ በዲቪ ይዞሽ ለሄደው ወንድማችንም ከልብሽ ሳይሆን ‹‹ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነው›› በማለት ጌታችን ከተናገረላቸው ሕዝቦች ጎራ ያስመድብሻል። ምክንያቱም አንቺም አጋርሽን በከንፈርሽ እያከበርሽ በአፍሽም እየወደድሽ በልብሽ ግን ከእርሱ በመራቅሽ ዋሽተሽዋልና ነው።

በቅዱስ ወንጌል እንደተጻፈው ትንሹ ልጅ ‹‹አባቴ ሆይ ከገንዘብህ የሚደርሰኝን ክፍል ስጠኝ አለው። አባትም ገንዘቡን ከፍሎ ሰጠው። ከጥቂት ቀንም በኋላ ታናሹ ልጅ ገንዘቡን ሁሉ ሰብስቦ ወደሩቅ ሀገር ሄዶ ከዚያም እያባከነ ገንዘቡን በተነ። ሁሉንም ካከሰረ በኋላ በዚያች አገር ጽኑ ረኀብ ሆነ እርሱም ይጨነቅ ጀመር። ሄዶም ከዚያች ሀገር ሰዎች ከአንዱ ጋር ተዳበለ እርሱም እሪያ (ዓሳማ) ሊያሰማራ ወደ ሜዳ ሰደደው።››

እሪያዎችም ከሚባሉት አስር ሊመገብ ይመኝ ነበር። የሚሰጠውም አልነበረም። ወደ ልቡም ተመልሶ እንዲህ አለ፡- እንጀራ የሚተርፋቸው የአባቴ ሞያተኞች ስንት ናቸው? እኔግን በዚህ በረኀብ እሠቃያለሁ። ተነሥቼም ወደ አባቴ እሄዳለሁና። አባቴ ሆይ በሰማይና በፊትህ በደልሁ ወደ ፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም ከሞያተኞችህ እንደ አንዱ አድርገኝ እለዋለሁ። ተነሥቶም ወደ አባቱ መጣ እርሱም ገና ሩቅ ሳለ አባቱ አየውና አዘነለት። ሮጦም አንገቱን አቀፈውና ሳመው። ልጁም አባቴ ሆይ በሰማይና በፊትህ በደልሁ ወደፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም አለው። አባቱ ግን አገልጋዮቹን አለ ፈጥናችሁ ከሁሉ የተሻለ አምጡና አልብሱት ለጣቱ ቀለበት ለእግሩም ጫማ ስጡ። የሰባውን ፊሪዳ አምጥታችሁ እረዱት። እንብላም ደስም ይበለን። ይህ ልጄ ሞቶ ነበርና ደግሞም ሕያው ሆኖአል። ጠፍቶም ነበር ተገኝቶአልም ደስም ይላቸው ጀመር።›› (ሉቃ.፲፭፥፲፪-፳፬)

ወለተ ገብርኤል ይህ ከአባቱ ቤት ጠፍቶ የነበረው ልጅ ወደ ልቡ ተመልሶ ለአባቱም አባቴ ሆይ በሰማይና በፊትህ በደልሁ ወደፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም በማለት መናዘዙን ልብ በዪ። ይህ ልጅ ከአባቱ ተለይቷል፣ ከአባቱም ቤት ወጥቷል፣ ከአባቱም ቤተሰብ ተለይቷል። የሁላችን አባት እግዚአብሔር ስለሆነ ስንጸለይ አባታችን ሆይ ብለን እንለምነዋለን።

ከአባቱ ቤት የጠፋው ልጅ በሰው ቤት አሽከርነት መግባቱ ሳያንስ የእሪያውን ምግብ እስከ መመገብ መድረሱን ልብ በዪ። ወለተ ገብርኤል የእሪያ ምግብ የተባለው የአሕዛብ ተግባር ነው። ኃብቻን እንደ ቀላል ነገር ተመልክተው ለፍቺ የሚነሳሱ እና በጋብቻ ላይ ጋብቻ የሚፈጽሙ አሕዛቦች ናቸውና።

እግዚአብሔር በሊቀ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ አድሮ ‹‹የአሕዛብን ፈቃድ ያደረጋችሁበት በመዳራትና በሥጋ

ምኞት የተመላለሳችሁበት ያለፈው ዘመን ይበቃናልና:: ›› (፩ኛ ጴጥ.፬፥፫) ብሏል:: ወለተ ገብርኤል መፋታት እግዚአብሔር የሚጠላው ዲያብሎስ የሚወደው ተግባር መሆኑን እና የአሕዛብ ተግባር መሆኑን በቅድሚያ መረዳት ይገባሻል::

ከአባቱ ቤት የጠፋው ልጅ ወደ ልቡ እንደተመለሰና ወደ አባቴ ቤት እመለሳለሁ ወደፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም በማለት ወስኖ ውሳኔውን ተግባራዊ ማድረጉንም ልብ በዪ ይህ ከአባቱ ቤት የጠፋው ልጅ ነፍሱ ከሥጋው ሳይለይ ነው ወደ አባቱ የመጣው አባቱም ገንዘቤን በትኖ፣ ስሜን አጉድፏል ብሎ ሳይጠላው ሩጦ አቅፎ እንደሳመው ቃሉ ይመሰክራል:: ልጁ በቁም የሞተ መሆኑንም አባቱ መስክሯል:: ይህ ልጄ ሞቶ ነበር እንዲል::

ሲመለስ ግን ሕያው ሆነ ተብሏልና:: ወለተ ገብርኤል ይህ የአንቺ ጉዞ ከአንድ ክርስቲያን የሚጠበቅ ተግባር አለመሆኑን በቅድሚያ ልትገነዘቢ ይገባል:: ለጠፋው ልጅ ከሁሉ የተሻለ ልብስ አምጥታችሁ አልብሱት አባቱ ማለቱንም አስተውይ:: ከሁሉ የተሻለው ልብስ የተባለው ንስሐ ነው፣ ስለዚህ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ላደረግሻቸውም፣ ላሰብሻቸውም ንስሐ ግቢ፣ ከዚያም ከሁሉ የተሻለ ልብስ መልበስሽን ማስታወስ ይገባሻል:: በጠቢቡ ሰሎሞን አድሮ እግዚአብሔር ‹‹ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል::›› (ምሳ.፳፰፥፲፫) ብሏል::

ወለተ ገብርኤል በቅድሚያ የገባልሽልን ሀሳብ ሁሉ እንደ አንድ ክርስቲያን ኃጢአት መሆኑን ልትረጂ ይገባል:: እርሱም ትዳርን ያህል ትልቅ ተቋም ለማፍረስ ማሰብና በጋብቻ ላይ ጋብቻን መመኘት በሕግ ወንጀል በሃይማኖትም ኃጢአት ነውና:: ስለዚህ አሁን ከአንቺ የሚጠበቀው በቅድሚያ የነፍስ አባት መያዝ፣ ከዚያም ንስሐ መግባት፣ ሀገር ውስጥ ለሚገኘው ለቀድሞ ጓደኛሽ የራሱን የትዳር አጋር እንዲፈልግና የራሱን ሕይወት እንዲመሠርት በግልጽ ንገሪው::

አንቺ ደግሞ የመሠረትሽውን ትዳር እውነተኛ ትዳር መሆኑን ከልብሽ እመኚ ከነፍስ አባትሽ ጋር ከተነጋገርሽ በኋላ አሁን አብረሽው ያለሽውን የትዳር አጋርሽን በግልጽ ነግረሽው ይቅርታ ጠይቂው:: ክርስቲያን በፈተናው ወቅት ወደ ቤተ ክርስቲያን እየገሠገሠ ችግሩን ለእግዚአብሔር ተናግሮ መፍትሔ እንደሚያገኝ እመኚ:: ዛሬ ከቤተ ክርስቲያንና ከጸሎት የለየሽ መንፈስ ነገ ደግሞ ወደ ክሕደት ሳይወስድሽ የመዳን ቀን ዛሬ ነው ተብሏልና በጸሎት በርቺ:: ከቤተ እግዚአብሔር አትለይ ስለ ደረሰብሽ ፈተና ደግሞ ገዳማዊያኑ አባቶቻችን እንዲጸልዩልሽ ሀገር ቤት ባሉት ቤተሰቦችሽ በኩል መባ በመላክ በጸሎት እንዲያስቡሽ አስደርጊ:: ምክንያቱም ‹‹የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች›› (ያዕ.፭፥፲፮) ተብሏልና::

ወለተ ገብርኤል ከአባቱ ቤት እንደጠፋው ልጅ አንቺም ወደ ልቡናሽ ተመልሰሽ ንስሐ ገብተሽ፣ ትዳርሽን አጽንተሽ ይዘሽ ክርስትናን በሕይወት እንድትኖሪ የእግዚአብሔር ቸርነት፣ የድንግል ማርያም ምልጃ፣ የቅዱሳን ጸሎት ይርዳሽ::